# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 327 ሐምሌ 27 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# በኢኮኖሚ ስኬታማ ለመሆን በአንድ ጊዜ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ማከናወን እንደሚገባ ተገለጸ

**ስምስም ምንግሥቱ**



ፎቶ - ዳኜ አበራ

<u>አዳማ፡-</u> በኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ውጤታማ ለመሆን አንድ ዘርፍ እስኪያድግ ጠብቆ ወደ ሚቀጥለው ዘርፍ ሽግግር ማድረግ ሳይሆን፤ በአንድ ጊዜ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ማከናወን እንደሚገባ የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር እዮብ ተካልኝ፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሰሞኑን በአዳማ ከተማ ባዘጋጀው ሰባተኛው ስለኢትዮጵያ የፎቶግራፍ አውደርዕይና የፓናል ውይይት ላይ እንደተናገሩት አንደኛው ዘርፍ ካደገ በኋላ የሚቀጥለው ዘርፍ እንዲቀበለው የማድረግ አካሄድ አዋጭ አይደለም፤ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርም አያስገኝም።

ለአብነትም የግብርናው ዘርፍ አድጎ ሀብት ካፈራ በኋላ ወደሚቀጥለው ዘርፍ ሽግግር ለማድረግ የሚደረግ ጥረት ከዚህ ቀደም የነበረ እሳቤ እንደነበረ የጠቆሙት ዶክተር እዮብ፤ በዚህ ወቅት ውጤታማ የሚያደርገው ግብርናውንም፣ ማዕድኑንም፣ የመረጃና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂውንም (አይሲቲ)እና ሌሎች ዘርፎችንም ያካተተ ዘርፍ ብዙ ተግባራትን ማከናወን ነው ብለዋል። በመሆኑም ከአንዱ ዘርፍ ወደሌላው ዘርፍ የሚደረገው ሽግግር በታለመለት መልኩ ማከናወን እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

የኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር ሊመጣ የሚችለው አሳታፊ የሆነና ሁሉንም የሚጠቅም የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት ሲቻል እንደሆነ የጠቆሙት ዶክተር እዮብ፤ በዜጎች፣ በክልሎች፣ በተቋማት መካከል ፍትሐዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል እና ፍትሐዊ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት መፍጠር ካልተቻለና ሁሉም ተያይዞ እንዲያድግ ካልተደረገ በስተቀር ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ያስቸግራል ብለዋል።

በኢኮኖሚ ስኬታማ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











ፎቶ - በፀሐይ ንጉሤ

# አገልግሎት አሰጣጡ ዲጂታላይዝ መደረጉ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን እንደሚረዳ ተጠቆመ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የኢንዱስትሪ ዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ ዲጂታላይዝ መደረጉ ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማስፈን እንደሚረዳ ተጠቆመ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ያለማውን የኤሌክትሮኒክስ

አገልግሎት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# ከበልግና መኸር ግብርና

## ከ16 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት እንደሚገኝ የባሌ ዞን አስታወቀ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> ከበልግና መኸር የግብርና ሥራዎች በአጠቃላይ ከ16 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት እንደሚገኝ በኦሮሚያ ክልል የባሌ ዞን ግብርናና የተፈጥሮ ሃብት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ አቶ አሊዬ መሐመድ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በዞኑ የበልግ ምርት እየተሰበሰበ ይገኛል። በክላስተር የለማው ምርት ተሰብስቦ ሲጠናቀቅ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ እንደሚገኝ ይጠበቃል።

ከመኸር ግብርናው ሥራ ደግሞ ከስንዴ ልማት ብቻ ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ የቢሮ ኃላፊው ገልጸዋል።

ባሌ ላይ በአሁኑ ወቅት ሁለት አይነት የግብርና ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል። በአንድ በኩል በቆላማ አካባቢዎች የደረሱ ምርቶችን የመሰብሰብ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በደጋማ አካባቢዎች የመኸር ግብርና ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። በአንድ በኩል ኮንባይነር ሲያጭድ በሌላኛው በኩል በትራክተር እየታረሰ ነው ብለዋል።

በበልግ ግብርና ሥራ 247 ሺህ 911 ሔክታር መሬት በተለያዩ ሰብሎች መሸፈኑን የገለጹት አቶ አሊዬ፤ ከዚህ ውስጥ 154 ሺህ ሔክታር በክላስተር የለማ የስንዴ ምርት መሆኑን አስረድተዋል።



አቶ አሊዬ መሐመድ

የደረሰው የበልግ ምርት በኮምባይነር እገዛ እየተሰበሰበ ይገኛል። ምርቱም እስከቀጣዩ አንድ ወር ድረስ ተሰብስቦ እንደሚያልቅ ይጠበቃል። በኋላም

ከበልግና መኸር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “አትሌቶቻችን በዓለም አደባባይ ባገኙት ድል ፍቅርን ያስገደብ አስተምረውናል”

**- አትሌት ገዛኸኝ አበራ**
**የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት**

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- አትሌቶቻችን በዓለም አደባባይ ላይ ባገኙት ድል ፍቅርን ያለገደብ አስተምረውናል ሲል የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት የሆነው አትሌት ገዛኸኝ አበራ ተናገረ፡፡

አትሌት ገዛኸኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ዘርና ሃይማኖት ሳይለዩ ባደረጉት መተጋገዝ ለድል በቅተዋል። በዚህ ድል ፍቅርንና አንድነትን ያለገደብ አስተምረዋል፡፡

አትሌቶች በተባበረ ክንድ ባስገኙት ድል ምክንያት ችግሮችን በጋራ ሆኖ በመሥራት ማለፍ እንደሚቻል አሳይተዋል። በድሉ አማካኝነት አንድነትና ፍቅር የተሻለ ውጤት እንደሚያበቁ ለመላው ኢትዮጵያዊ መስበክ ችለዋል ሲል ተናግራል።

ድሎቹ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያውያን ድል ነው ያለው አትሌት ገዛኸኝ፤ ፌዴሬሽኑና አትሌቶቹ አንድ ላይ በመሆንና በመተጋገዝ ያለማንም ጣልቃገብነት ሥራቸውን በመሥራታቸው ውጤታማ መሆናቸውንም ገልጿል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በየቦታው ችግሮች ላይ በሚገኝበት ወቅት ጀግኖች አትሌቶች አንድነትን ያሳዩነት መንገድ ለበርካቶች ትምህርት የሚሰጥ ነው። አትሌቶቹ በዓለም አደባባይ ዕድሜ፤ የብሔርና የግል አስተሳሰብ ሳይለያያቸው በመተባበር ላሳዩት አርአያነት ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል ብሏል።

አትሌት ገዛኸኝ አትሌቶቻችን በጠንካራ የቡድን መንፈስ የተጎናፀፉትን ድል በሌሎችም መስኮች መድገም እንደሚያስፈልግም ነው መልዕክቱን አስተላልፏል።

የማራቶን አትሌቶች ቡድን መሪ መሆኑን የገለጸው አትሌት ገዣኸኝ፤ ኢትዮጵያ በሁለቱም ፆታዎች በዓለም አትሌቲክስ ውድድሩ በማራቶን ያገኘችው ድል አንፀባራቂ መሆኑን በመጠቆም ፤ አትሌቶቹ ከዚህ ቀደም ልምምድ የሚያደርጉት ተበታትነው እንደነበር አስታውሷል።



አሁን ላይ ግን በአብሮነት ልምምድ በመሥራትና በመቆየታቸው ለድል መብቃታቸውን አስረድቷል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተተኪዎችን ማፍራት ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ የገለፀው አትሌት ገዛኸኝ ክለቦችን እንደ አዲስ በማጠናከር ላይ እንደሚገኙም ጭምር ነው የገለፀው፡፡

በኮሎምቢያ በመካሄድ ላይ በሚገኘው ከሃያ ዓመት በታች ሻምፒዮና ላይ የተገኘው ድል ፌዴሬሽኑ ተተኪዎችን ማፍራት ላይ ሥራዎች በመሥራት ላይ እንደሚገኙ ያመላከተ መሆኑን የገለፀው አትሌቱ፤በተለያዩ ክልሎች ላይ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ የመከታተልና የመደገፍ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ተናግሯል፡፡

በአሜሪካ ኦሪገን በተካሄደው 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ በአራት የወርቅ፣ አራት የብር እንዲሁም ሁለት የነሐስ በድምሩ አስር ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ከትላንት በስቲያ ሌሊት ውድድሯን ከአሜሪካ በመከተልና ጃማይካን በማስከተል በዓለም ሁለተኛ እና በአፍሪካ በአንደኝነት ማጠናቀቋ የሚታወስ ነው።

በኮሎምቢያ በመካሄድ ላይ በሚገኘው ከሃያ ዓመት በታች ሻምፒዮና ላይ ይህ ዘገባ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አንድ ወርቅና አንድ ብር አግኝታለች። ፡

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከሰሞኑ በተደጋጋሚ እያስገኙ ባሉት ድል ደስታ ተሰምቶኛል ያለው አትሌት ገዛኸኝ፤ ለመላው የሀገሪቱ ዜጎችም የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

## አገልግሎቱ ያካሄደው መድረክ የቀጣናውን ሠላም ማረጋገጥ የሚያስችል ግብዓት እንደተገኘበት ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ያካሄደው ሥልጠናዊ ግምገማ ተለዋዋጭ የደኅንነት ስጋት በተደቀነበት የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የኢትዮጵያን ሰላም ለማረጋገጥ የሚያስችል ግብዓት እንደተገኘበት ተገለፀ

አገልግሎቱ ለአራት ቀናት ያካሄደውን ሥልጠናዊ ግምገማ አጠናቋል፡፡

አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ መድረኩን አስመልክቶ ለኢፕድ በላከው መግለጫ እንዳመለከተው፤ የተቋሙ መካከለኛና ከፍተኛ አመራሮች ከተሳተፉበት አመታዊ የአፈጻጸም ግምገማ ጎን ለጎን በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ፣ ቀጣናዊ፣ ሀገራዊና ተቋማዊ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

በላቀ ተቋማዊና የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ዙሪያ፤ በሥነ ልቦና ጦርነት ንድፈ ሐሳብና ተሞክሮዎች፤ በተሻሻለው ዐዋጅ አተገባበር፤ በዓለም አቀፋዊ፣ ቀጣናዊና ሀገራዊ የደኅንነት ስጋቶችና መልካም አጋጣሚዎች እንዲሁም በሌሎችም ወቅታዊ የመረጃና ደኅንነታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትኩረት ያደረገው ሥልጠና ተለዋዋጭ የደኅንነት ስጋት በተደቀነበት የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የኢትዮጵያን ሰላም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ግብዓቶች እንደተገኙበት መግለጫው ጠቁሟል፡፡

አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ በተያዘው በጀት ዓመት ያቀዳቸውን የመረጃና የደኅንነት ተልዕኮዎች በላቀ ደረጃ ለመፈጸም እገዛ እንደሚያደርግም አመልክቷል፡፡

በፍጥነት ተለዋዋጭ የሆነውን ዓለም አቀፋዊ ፣አካባቢያዊና ሀገራዊ ሁኔታዎች በተመለከተ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተንና ለአስፈጻሚ አካላት በማቅረብ እንዲሁም ቴክኖሎጂዎችን ለተለያዩ ስምሪቶች በማዋል የደኅንነት ስጋቶችን በከፍተኛ ደረጃ ለማስቀረትም ዝግጅት መደረጉ የተረጋገጠበትና ቀጣይ አቅጣጫ የተቀመጠበት ሥልጠናዊ ግምገማ እንደነበርም የአገልግሎት መሥሪያ ቤቱ መግለጫ አብራርቷል፡፡

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ተልዕኮውን ከወቅታዊ ሀገራዊ የደኅንነት ስጋት አንጻር በመቃኘት እንዲወጣ ሥልጣንና ኃላፊነት የሚሰጠው የማሻሻያ ዐዋጅ ባለፈው የበጀት ዓመት መጽደቁ ከፍተኛ አቅም እንደሚፈጥር በሥልጠናዊ የግምገማ መድረኩ ተብራርቷል፡፡

# ዲያስፖራው ስለሀገራዊ ምክክሩ በቂ መረጃ እንዲኖረው ማድረግ እንደሚገባ ተጠቆመ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ዲያስፖራውን በኤምባሲዎች በኩል ስለሀገራዊ ምክክሩ በቂ መረጃ እንዲኖረው ማድረግ እንደሚገባ በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ገለፁ።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት እና የኢድ እስከ ኢድ ብሔራዊ ኮሚቴ በጋራ ያስተባበሩት “በሀገራዊ ምክክር የዲያስፖራው ሚና እና የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ” በሚል ርዕስ ከዲያስፖራው ማኅበረሰብ ጋር ሰሞኑን ምክክር ሲካሄድ ዲያስፖራዎች እንደገለጹት፤ ዲያስፖራውን በኤምባሲዎች በኩል ስለሀገራዊ ምክክሩ በቂ መረጃ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህም አገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ማድረግ ይገባል።

በውይይቱ ላይ ተሳታፊ ከነበሩት መካከል አንዱና የዓለም አቀፍ ወጣቶች ኅብረት መሥራችና ፕሬዚዳንት የሆነው የካሊፎርኒያ ነዋሪ ወጣት ቢኒያም ጌታቸው እንዳለው፤በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ሁሉም ተሳታፊ እንዲሆን ያስፈልጋል። በዘር በኃይማኖት እና በሌሎችም ዘርፎች ብዙ ዓይነት ልዩነቶች ያሉባት ሀገር በመሆኗ ሀገራዊ ምክክሩ እነዚህን ያካተተ እንዲሆን ይጠበቃል። ሁሉም በምክክሩ የራሱን በጎ አስተዋፅዖ ለማድረግ መዘጋጀት ይኖርበታል።

ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬት ብዙ ተከታይ ያላቸውን የማኅበራዊ ገፅ ጸሐፊያን እና ዩቲዩበሮችን አቅርቦ ማነጋገር እንደሚያስፈልግም ተናግሯል።

ሀገርን ለማስቀጠል እና ለልጅ ልጆቻችን የምትተርፍ ኢትዮጵያን ለመገንባት ዲያስፖራዎች እያደረጉት ላለው ተጋድሎ ትልቅ ክብር አለኝ ያለው ወጣት ቢኒያም፤ በሀገራዊ ምክክሩ ላይም ንቁ ተሳትፎ ልናደርግ ይገባል ብሏል።

ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑም ዳያስፖራውን ማኅበረሰብ በያለበት ሊያገኝበት የሚችል መንገድ በኤምባሲዎች በኩል ማመቻቸት እንደሚኖርበት



ቢኒያም ጌታቸው



ማርታ ጌቱ



አቶ ቦሀንድ አህመድ

ጠቁሟል።

ሌላው የውይይቱ ተሳታፊ የነበሩት የዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ነዋሪው አቶ ቦሀንድ አህመድ በበኩላቸው፤ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሀገራቸው ጉዳይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንደሚመለከታቸው ገልፀው፤ ዲያስፖራውን የዚህ ሀገራዊ ምክክር አካል ማድረጉ ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል።

በለውጡ ማግሥት ጀምሮ የተሠራው ሥራ በርካታ ዲያስፖራዎች ከኤምባሲያቸው ጋር ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖራቸው እና ወደ ሀገራቸው እንዲመጡ አድርጓቸዋል የሚሉት አቶ ቦሀንድ፤ ይህ በሀገር ላይ ትልቅ ለውጥ እንዲያመጣ ተስፋ የሚጣልበት እንደሆነ ገልፀዋል።

እንደ አቶ ቦሀንድ ገለፃ፤ ሀገራዊ ምክክሩ ላይም በኤምባሲዎች አካባቢ በተግባር መሠራት አለበት። ዲያስፖራው እንዲወያይ በተደረገ ቁጥር ያለውን አሉታዊ አስተሳሰብ ይቀንሳል። በመሆኑም በኤምባሲዎች አካባቢ ዲያስፖራው የሚወያይበትና ግንዛቤ የሚጨብጥበት መንገድ ለመፍጠር የሀገራዊ ምክክር ሥልጠና እና ሌሎች ድጋፎችን በማድረግ ሊሠራ ይገባል። ዲያስፖራውን አሳትፎ መሥራት ከተቻለ ሀገራዊ ምክክሩን ውጤታማ ማድረግ ይቻላል።

ሰሜን አሜሪካ ሚኒሶታ ነዋሪዋ ወጣት ማርታ ጌቱም፤ ከላይ የቀረቡትን አብዛኞቹን ሀሳቦች ትጋራለች።

በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ እንደምታደርግ የገለፀችው ወጣት ማርታ፤ ለውጡን ተከትሎ እንደ አብዛኞቹ ዲያስፖራዎች መንግሥትን ከመቃወም በቀጥታ ወደ ደጋፊነት እንደተሸጋገረች ገልፃለች።

ከምንም በላይ የኢትዮጵያን ዘላለማዊነት እደግፋለሁ የምትለው ወጣት ማርታ፤ ዲያስፖራው በሀገራዊ ክንውኖች ላይ መረጃ ስለሌለው ለግራ መጋባት እየተዳረገ ነው። ይህ በሀገራዊ ምክክሩ ላይም የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳያመጣ የግንዛቤ መፍጠሪያ መንገዶችን አሟጦ በመጠቀም ሀገራዊ ምክክሩ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ ይገባል።

ወጣት ማርታ፤ በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በብሔርና በሀይማኖት ልዩነት ተጠቅሞ ግጭት ለመፍጠር የሚደረግ እንቅስቃሴ ይታያል ፤ በሀገሪቱ የጋራ ታሪክ ላይም መግባባት ላይ ስላልተደረሰ ይህንን ነገር ወደ አንድ እልባት ለማምጣት ሀገራዊ ምክክሩ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ከሀገራዊ ምክክሩንም ሆነ ኢትዮጵያን ለሚቃወሙ አካላትን በኤምባሲዎች በኩል ተደራሽ በማድረግ እነሱንም ማዳመጥ ይገባል ስትል ገልፃለች።

በተካሄደው ውይይት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ በኮሚሽነሮቹ በኩል የተጣለበትን ኃላፊነት አስመልክቶ ማብራሪያ ተሰጥቷል። የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳዩ እና የኢትዮጵያን አሁናዊ ሁኔታ የሚያስዳስሱ የውይይት መነሻ ሰነዶችም ቀርበዋል።

# እምባዎችን ለማበስ የተዘጋጀው በጎ ተግባር

**ውብሸት ሰንደቁ**

ኢትዮጵያ በለውጡ መንግሥት አዲስ የለውጥ ጎዳና ላይ ብትወጣም ከትርክቶች ተላቃ ከዘር መድሎ እንዳትርቅ አጥፊዎች እየተገዳደሯት ይገኛሉ። በነዚህ አጥፊዎች ምክንያትም ልማትን የምትሻ ሀገር ተገድዳ ጦርነት ውስጥ ገብታለች፤ ለሕዝቦቿ መረጋጋት ስትታትርም በአጥፊ ኃይሎች ሴራ ሕዝቦቿ ለመፈናቀልና ለመገደል ሰርክ እየታጩ ይገኛሉ።

ይህን የሰሙና ያዩ ምዕራባውያንና ሌሎች የኢትዮጵያን ሰላም የማይፈልጉ ሀገራት ክስተቶቹን እንደ መልካም ግብዓት ተጠቅመው ለሥም ማጠልሻና ለፖለቲካ አጀንዳ ማሟሻ ተጠቅመውበታል። አልፎም ረጃጅም እጆቻቸውን ተጠቅመው በሕቡዕና በግልፅ ለነውጧ ሲቆምሩ ታይተዋል። አብዛኞቹ ሀገራትም የበሬ ወለደ ተረታቸውን በሚዲያዎቻቸው ዘመቻ ጋሻ ጃግሬነት እያስነዙ መበተኗን ለማቅረብ ሽር ጉድ ሲሉ ከርመዋል።

ኢትዮጵያ በማይናወጥ መሠረት ላይ የተቀመጠች ሀገር ሆነችና አሁን ወደ ቀደመ ሰላሟ ወደመመለስ ላይ ትገኛለች።

እውነትና ንጋት ይሉት ሃቅ የአህያ ሆድ እየመሰለ መጥቷል።

ለሕሊናቸው የተገዙ ዕውነታውን እየዘገቡ፤ የችግሩን መፍቻ ቁልፍ ተባብረው ሲያፈላልጉ የቆዩም አልጠፉም፤ የክፉ ቀን ቁርጠኛ ወዳጆች።

ታዋቂው አሜሪካዊ ጀማል ካውንተስ በሰሜኑ ጦርነት እና በሌሎች ጊዜያትም ኢትዮጵያ ውስጥ እውነቱን ያዩ ፎቶ ጋዜጠኛ ነው። በጦርነቱ እና በግጭት ምክንያት የተጎዱ ዜጎችን በደል ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዕውነታውን ለማስገንዘብና ድጋፍ ለማሰባሰብ ከኦገስት 4 እስከ 7 ቀን 2022 ድረስ ኤግዚቢሽን በሀገረ አሜሪካ ሎስ አንጀለስ ከተማ ለማካሄድ ወጥኗል። በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የተለያዩ ቦታዎች እና በካናዳ እንዲሁም ወደ አውሮፓ በማቅናት የፎቶ ግራፍ ኤግዚቢሽን



ጀማል ካውንተስ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ፎቶዎች በማንሳት እውነታው ለዓለም አስተዋውቋል፤

እንደሚካሄድም ፎቶ ጋዜጠኛው በዕርዳታ ማሰባሰቢያ የበይነ መረብ ገፁ አሳውቋል።

ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በአማራ ክልል በተለያዩ የተፈናቃዮች ካምፖች ላይ ያየውን ሰቆቃና በስቃይ የተሞላ ሕይወት ተመልክቷል። በኢትዮጵያ ለ16 ወራት ዘልቆ የቆየውን የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ጦርነት በተፈናቃዮች፣ በሲቪሎች ስቃይ እና በሕይወት ያስከፈለው ዋጋም የአይን እማኝ ሆኖ አይቷል። በጦርነትና በዘር ማፅዳት ምክንያት አካባቢያቸውን ጥለው ለመሄድ የተገደዱና የተፈናቀሉ ዜጎችን መከራ ያየው ታዋቂው የአሜሪካ ፎቶ ጋዜጠኛ ጀማል ካውንተስ "የወለጋ ዕምባዎች" (Tears of Wollega) በሚል ርዕስ ዐውደ ርዕይ በማዘጋጀት ገቢ ለማሰባሰብ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

ፎቶ ጋዜጠኛው ብዙም ያልተዘገበ እና የተሳሳተ መረጃ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች አንዱ በኦሮሚያ ክልል በወለጋ ተዋልደውና ተጋምደው በሰላም ይኖሩ የነበሩ ሰላማዊ የአማራ ተወላጆች ላይ የተፈጸመው የጅምላ ግድያ ነው ሲል ገልጿል። በአለፉት ዓመታት በአካባቢው የተነዛው የፀረ አማራ ፅንፈኞች ፕሮፖጋንዳ ብሔርን መሠረት አድርጎ ወደሚፈፀም ግድያ አምርቷልም ነው ያለው።

በወለጋ ከደረሰው የሸኔና ተባባሪዎቹ ታጣቂዎች ጥቃት ያመለጡት የአማራ ተወላጆች በአማራ ክልል የተለያዩ ቦታዎች በተፈናቃዮች ድንኳኖች አሳዛኝ ሕይወትን እየተጋፈጡ ለመኖር ተገደዋል የሚለው ጀማል ካውንተስ፤ የአማራና የአፋር ክልሎችን በመጎብኘት በተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች የሚኖሩትን ዜጎችም ሁኔታ እንደተመለከተ ገልጿል።

ስለዚህ ጉዳይ መመስከር እና ዕውነታውን ማውጣት ይህን እየጨመረ የመጣ የሰው ልጆች ስቃይ ለመግታት ያግዛል ብዬ በማመኔ ይህን ኤግዚቢሽን ለመጀመር አነሳስቶኛል የሚለው ጀማል ካውንተስ፤ ወደ ወሎ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ባደረግሁት ተደጋጋሚ ጉዞ በሰበሰብኳቸው የፎቶና ሌሎች መረጃዎች በሚዘጋጀው የፎቶ እና የምሥክርነት ኤግዚቢሽን ለተፈናቃዮቹ ወዳሉበት የሚላኩ ልገሳዎችን ለማሰባሰብ በማሰብ ነው ብሏል። እኔ እንደማስበው ይላል ፎቶ ጋዜጠኛው፤ እኔ እንደማስበው ዐውደ ርዕዩ በወሎ አማራ ክልል ከሀይቅ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ የተፈናቃዮች ካምፕ ውስጥ የተፈናቀሉ ዜጎች እየደረሰባቸው ያለውን አሰቃቂ ሁኔታ ግንዛቤ ያሳድጋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ሲል ይገልፃል።

እንደ ፎቶ ጋዜጠኛው ገለፃ፤ በዚህ ካምፕ ውስጥ በሕይወት የተረፉ ሰዎች የቤተሰብ አባሎቻቸው ሲገደሉ ያዩ ናቸው። የማኅበረሰቡ አባላት ሲገደሉ እና ሌሎች ጥቃቶችን አይተዋል። እንዲህ ሲሆን እያዩ በተዓምር ተርፈው ነው ዕድለኛ ሆነው ለማምለጥ የበቁት። አንዳንዶቹ ከሞት ለማምለጥ እስከ 22 ቀናት ድረስ በእግራቸው ለመጓዝ ተገድደዋል።

ዐውደ ርዕዩን ለማዘጋጀት የተነሳሳሁት ስለሁኔታውና ስለጉዳዩ ለማሳወቅ ብቻ አይደለም የሚለው ጀማል ካውንተስ ቅን ልባዊ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች ተባብረው እና የራሳቸውን አስተዋፅዖ ጨምረውበት በሰላማዊ ዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት እንዲቆም ለማድረግ ነው። በተጨማሪም የሚመለከተው የመንግሥት አካላት ምላሽ እንዲሰጥና ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ለማድረግ ስለምፈልግ ነው። አሁንም እንደልባቸው ወጥቶ መግባት የማይችሉ እና የጥቃት ስጋት ያለባቸው ሰዎች በርካታዎች ናቸውና ብሏል።



# የተፈጥሮ ጥበቃ ሥራው የአየር ንብረት ለውጥ እንዲመጣ እያደረገ መሆኑ ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> በኢትዮጵያ በተሠራው ጠንካራ የተፈጥሮ ጥበቃ ሥራ የደን ሽፋን መሻሻል በማሳየቱ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ውጤት እየመጣ መሆኑን የዕጽዋት ሳይንስ ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ይተብቱ ሞገስ አስታወቁ።

የዕጽዋት ሳይንስ ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ይተብቱ ሞገስ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ አረንጓዴ አካባቢዎች ትነት ስለሚኖራቸው ተጨማሪ እርጥበትን ይፈጥራሉ፤ ይህ ደግሞ የዝናብ መጠን እንዲጨምር ያደርጋል።

ከባህር ከሚመጣው ትነት ጋር በመሆኑ ድርቅን የመቀነስና ዝናባማነትን የመጨመር ሁኔታ ይፈጥራል ያሉት ዶክተር ይተብቱ፤ ነገር ግን በቅርቡ የተተከሉ ችግኞች አሁን የሚታየውን የአየር ንብረት ለውጥ አምጥተዋል ለማለት ጥናት ማድረግ እንደሚጠይቅ ገልጸዋል።

ከኢትዮጵያ ሚሊኒየም ጀምሮ የደን ተከላ መጀመሩን ያስታወሱት ዶክተር ይተብቱ፤ በዚህም የደን ሽፋን መሻሻል እንዳለ ጠቁመዋል። የተጎዱ አካባቢዎች በተፈጥሮ ጥበቃ እንዲያገግሙ የማድረግ ሥራም የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ እንዲመጣ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ይተብቱ ገለጻ፤ የደን ሽፋን ሲኖር ትነት ይኖራል፤ ይህም ከባህር ከሚመጣው ትነት ጋር ተቀላቅሎ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንዲዘንብ ያግዛል። በሀገራችን ከሚሊኒየም ጀምሮ በተለይ ባለፉት አራት ዓመታት የተተከሉ ችግኞች የአየር ንብረት ለውጥ እያመጡ ቢሆንም አሁን የሚታየውን የዝናብ መጠንከር ከዚህ ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ለመናገር ጥናት ያስፈልጋል።

ከዓመት ዓመት በተለያየ ምክንያት የአየር ንብረት ለውጥ መምጣት፣ የንፋስ አቅጣጫ መቀያየርና የፀሐይ መጠንከር ተደማምረው የአየር ንብረት ለውጡ ላይ ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይችላል ያሉት ዶክተር ይተብቱ፤ ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ሁኔታ መቀያየርም አሁን ላለው ከፍተኛ የዝናብ መጠን መንስኤ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

እንደ ዕጽዋት ሳይንስ ባለሙያው ማብራሪያ፤ ከችግኝ ተከላው ባሻገር ከሰው፣ ከእንስሳትና ከመሳሰሉት አካላት ንክኪ ተጠብቀው የተከለሉ አካባቢዎች ከፍተኛ ውጤት እያመጡ ነው። በተለይ በሰሜን ሸዋ፣ በደቡብ ወሎ፣ በትግራይ እና በሐረርጌ ቀደም ሲል በጣም የተጎዱ አካባቢዎች ሲሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደረገው ጥበቃ ተቀይረዋል፤ በደን ተሸፍነዋል። ይህ ደግሞ የዝናብ መጠን እንዲጨምር ያደርጋል።

# የዋጋ ግሽበቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል በፖሊሲ የተደገፈ አሠራር ሊኖር እንደሚገባ ተገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> እንደ አገር የዋጋ ግሽበቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል በፖሊሲ የተደገፈ አሠራር ሊኖር እንደሚገባ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማኅበር የምርምርና የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ ተንታኝ ገለጹ።

የኢኮኖሚ ተንታኙ ዶክተር ደግዬ ጎሹ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሦስት አስርተ ዓመታት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ወደ ገበያው የሚለቀቀው የገንዘብ መጠን ኢኮኖሚውን የዕድገት ደረጃ ግንዛቤ ያላስገባ ነበር። ኃላፊነት የሚሰማው የመንግሥት አስተዳደር ያደርገዋል ተብሎ የማይጠበቅ እስከ 44 ነጥብ 4 በመቶ የሚሆን የሀገሪቷን ኢኮኖሚ የሚያክል ገንዘብ በዓመት ወደ ገበያ ይለቀቅ ነበር። ይህም በዋጋ ግሽበቱ ላይ አሉታዊ ሚና አሳድሯል።

በተጨማሪም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከፍተኛ ሁኔታ ሙስና ተንሰራፍቷል። ከ10 ዓመት በፊት ዝቅተኛ ሙስና ካለባቸው አገሮች ተመድባ የነበረችው ኢትዮጵያ ከ1997 በኋላ ሙስና ደረጃ ወጥቶለት የሚሠራ ሥራ ሆኗል። ሙስና ተስፋፍቶ የሚገኝባቸው 15 የሚደርሱ ተቋማት የተለዩ ሲሆን ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ሙሉ ለሙሉ የሚያጠፋ ስለሆነና አለመመጣጠንን የሚያሰፍን በመሆኑ ከፍተኛ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል ሲሉ የምጣኔ ሀብት ተንታኙ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ደግዬ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ከዓለም በተለየ ሁኔታ የባንክ የቁጠባ የወለድ ምጣኔና የብድር ወለድ ምጣኔ ተመጣጣኝ አይደለም። ቁጠባን የማያበረታታ፣ ሕዝቡ ገንዘቡን ባንክ ማስቀመጥ የማይችልበት የወለድ ምጣኔ ነው፤ ምን አልባት ገንዘቡን የሚስቀምጠው ሌባን ከመፍራት ነው። ስለዚህ ባንኮችን ይጠቅም ካልሆነ በስተቀር ኢኮኖሚውን የሚጠቅም አይደለም። በተቃራኒው የብድር ምጣኔው ወለድ ዝቅ ቢል ሰው የሚበደርበትና ሠርቶ የሚቀየርበት ሁኔታና ኢንቨስትመንትን የሚያሳድግበት ሁኔታ ይፈጥራል።



ፎቶ - በጸሐይ ገጉቤ

ዶክተር ደግዬ ጎሹ

ስለዚህ ይህ መሻሻል አለበት ብለዋል።

ዶክተር ደግዬ፤ 90 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረው ከውጭ በመጣ ስንዴና ዱቄት በተጋገረ ዳቦ አይደለም። የዱቄት ፋብሪካዎች ማምረት ቢያቆሙ 15 በመቶ የሚሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ነው ሊጎዳ የሚችለው እንጂ እንደ ግብጽና ሱዳን በዳቦ ምክንያት መንግሥት እስከ መገልበጥ የሚያደርስ አይደለም። ትልቁ አሳሳቢ ጉዳይ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋሙ ብዙ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች ሥራ ካቆሙ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ከ12 የማያንሱ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች ውስጥ ስምንት የሚሆኑት ሥራ የጀመሩ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች አሉ። እነሱ የሚጠቀሙት ግብዓት ካላገኙ ሥራ ያቆማሉ፤ እነዚህ አቆሙ ማለት የሚቀጥለው ዓመት ችግሩ የከፋ ስለሚሆን የዋጋ ግሽበቱን የሚቆጣጠር በፖሊሲ የተደገፈና እርምጃዎችን የሚገመግም አካል ሊኖር ይገባል ብለዋል።

ዜና

# የአራት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር የታክስ ቅሬታዎች እንደቀረቡለት ኮሚሽኑ አስታወቀ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት የአራት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር ግምት ያላቸው የጉምሩክና የገቢዎች ታክስ ቅሬታዎች እንደቀረቡለት የፌደራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ገለጸ።

ኮሚሽኑ የ2014 ማጠቃለያ ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማና የ2015 መሪ ዕቅዱን ትናንትና ይፋ ሲያደርግ የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ ሙሉጌታ አያሌው እንደገለጹት፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከደረሱት 1069 መዝገቦች መካከል 645ቱ ከጉምሩክ ጋር የተያያዙና የሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ዋጋ አላቸው።

ቀሪዎቹ ቅሬታዎች ደግሞ ከሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው ከገቢዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች መሆናቸውን ጠቁመው፤ በአጠቃላይ ከአራት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር በላይ የሚንቀሳቀስባቸው ቅሬታዎች ቀርበው እንደነበር ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሙሉጌታ ገለፃ፤ ኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት ከቀረቡለት ቅሬታዎች መካከል ለ719ኙ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ቀጥሮ ለ715 መዝገቦች ውሳኔ ሰጥቷል።

በጉምሩክ ኮሚሽንና ገቢዎች ከፍተኛ ታክስ ተጥሎብናል የሚሉ የግብር ከፋዮችን ቅሬታ ለማድመጥ የተቋቋመው የፌደራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ከተቋቋመበት ሐምሌ 2010 ጀምሮ ከ3600 በላይ መዝገብ ቅሬታ እንደደረሰው ተገልጿል።

ኮሚሽኑ ቅሬታዎችን በመቀበል ጉዳዮችን እያጣራ ውሳኔ እየሰጠ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ተናግረው፤ በቀጣይም የይግባኝ ሥርዓቱን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ፣ የአሠራር ሂደቱን ለማዘመን እና ቅሬታዎችን በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ ተፈፃሚ ለማድረግ ኮሚሽኑ ይበልጥ ጥረት እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

የኮሚሽኑ ጠንካራ ጎኖች በቀጣይ አጠናክሮ መሥራት እንደሚጠይቅም ጠቁመው፤ በተለይም ሙስናን ለመከላከል የተቋሙ ሠራተኞችን የንብረት ምዝገባ እንዲያያከናውኑ እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ለኪራይ ሰብሳቢነት ተጋላጭ የሆኑ ዘርፎችን በመለየት ችግሮች እንዳይከሰቱ የመከላከል ሥራ በመከናወን ላይ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

የኮሚሽኑ የፕላንና ለውጥ ማስተባበሪያ ዳይሬክተር አቶ እዮብ አለማየሁ በበኩላቸው ኮሚሽኑ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና የቀጣይ ዕቅዱን ማቅረቡ ጠንካራ ጎኖች በማጠናከር ክፍተቶችን ለመሙላት ያስችለዋል ብለዋል።



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

አቶ ሙሉጌታ አያሌው

ተገልጋዮች የኮሚሽኑን የአገልግሎት አሰጣጥ ግንዛቤ ተፈጥሮላቸው በተሰጣቸው አገልግሎት መርካታቸውን ከተገልጋዮች የተገኘው ግብረ መልስ እንደሚያሳይም አቶ እዮብ ገልጸዋል፡፡

ኮሚሽኑ የመገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም የተቋሙ ሥራዎች ለኅብረተሰቡ እንዲደርሱ እየሠራ እንደሆነ የገለጹት አቶ እዮብ፤ የአሠራር ግልፅነትንና የተገልጋዮችን እርካታን ለማሳደግ የሠራተኞችን የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱንም አመላክተዋል፡፡

ያለፈውን በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ በመገምገም በቀጣይ 2015 በጀት ዓመት ውስንነቶችን በማረም ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።



# ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን በጸጥታና ደህንነት ጉዳዮች በይበልጥ በጋራ ለመሥራት ምክክር አደረጉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን የተመራ የኢትዮጵያ የልዑክ ከደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ማያርዲት ጋር ተወያየ።

ምክክሩ የጸጥታና ደህንነት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፤ ልዑኩ በሁለትዮሽ ጉዳዮች ዙሪያ ከፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ጋር ውጤታማ ውይይት ማድረጉን አምባሳደር ሬድዋን በማኅበራዊ ትስስር ገፃቸው አስታውቀዋል።

ሀገራቱ ወንጀሎችን በጋራ መከላከል፣ ትብብርን ማሳደግና የደህንነት መረጃ መለዋወጥ በሚችሉበት ጉዳዮች ላይ መክረዋል።

# አገልግሎት አሰጣጡ ዲጂታላይዝ መደረጉ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አገልግሎት መስጫ ሥርዓት ትናንትና በይፋ አስጀምሯል። የዲጂታል አገልግሎቱ በዘላቂነት እንዲቀጥል የሚረዳ የትብብር ስምምነት በተቋማቱ መካከል ተፈርሟል።

በወቅቱ የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ ተጠያቂነትን ከማስፈን ባለፈ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ያግዛል።

ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ እንድትሆን ዘመኑ የሚጠይቀውን የዲጂታል አገልግሎት በአግባቡ መተግበር ይጠበቅብናል። ይህም ጊዜና ገንዘብን በመቆጠብ ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀምና የአገልግሎት አሰጣጡም ቀልጣፋ ለማድረግ ያስችላል ብለዋል፡፡

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ማድረግ የአምራች ኢንዱስትሪውን ለማሳደግና የውጭ ባለሀብቶችን ለመሳብ አገልግሎት አሰጣጡን ማዘመን ስለሚያስፈልግ ይህ የኦንላይን አገልግሎት መጀመሩን ጠቁመዋል።

የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት አሰጣጡ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ተወዳዳሪነትና ዘላቂ ዕድገት የሚወስን ብሎም የዘርፉን መዋቅራዊ ሽግግር የሚያሳድግ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በተጨማሪም ጥራትን በመጨመር፣ የአገልግሎት ተደራሽነትን በማሳደግና ግልጽ አሠራርን በማስፋፋት ዘርፉ ለአገር ዕድገት የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የሚያግዝ መሆኑንም ገልጸዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ በበኩላቸው፤ የለሙት የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት መስጫ ሥርዓቶች አገልግሎቶችን በማዘመን ምርታማነትን በመጨመርና ቁጥጥርን በማጠናከር ረገድ ፋይዳቸው የጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

ካሉበት ሆነው ሥራዎችን በቀላል መንገድና በቅልጥፍና መከወን ግድ የሚልበት ጊዜ ላይ እንገኛለን ያሉት ዶክተር በለጠ፤ በተቋማቱ ትብብር የለሙት የዲጂታል ሥርዓቶችም ሰዎች ካሉበት ሆነው የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች እንዲያገኙ በማገዝ ጊዜና ጉልበትን የሚቆጥቡ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚወዳደሩት ዓለም ላይ ካሉ አምራቾች ጋር በመሆኑ ራስን ከዓለም ጋር ለማራመድ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለመሆን የቴክኖሎጂ ሥርዓትን ማዘመን ይገባል ብለዋል።

በዚህ ረገድ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያስጀመረው የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት መስጫ ሥርዓት ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥና በተገልጋዮቹ ዘንድ ተመራጭ እንዲሆን የሚያግዘው መሆኑን ገልጸዋል።

የዲጂታል አገልግሎቱም ውጤታማ ሆኖ እንዲቀጥል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ በበኩላቸው፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት በየደረጃው ያሉ የመንግሥት ተቋማት አገልግሎታቸውን ዲጂታላይዝ እንዲያደርጉ እየሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

ይፋ የተደረገው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት ዜጎች የሚፈልጉትን አገልግሎት ያለምንም ውጣ ውረድ ባሉበት ሆነው እንዲያገኙ ያስችላቸዋል ብለዋል።

የኤክስፖርት ቀረጥ ማበረታቻ የምስክር ወረቀት፣ የቀረጥ ተመላሽ፣ የወጪ መጋራት፣ ገቢዎች ልዩ ልዩ አገልግሎት፣ ቅሬታዎችን መቀበልና ምላሽ መስጠት፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ምዝገባ አገልግሎት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኦንላይን ከሚሰጡ አገልግሎች መካከል መሆናቸው ተጠቅሷል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት www.eservices.gov.et ላይ ማግኘት እንደሚቻል ተገልጿል።

# በኢኮኖሚ ስኬታማ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሙሉውን ማኅበረሰብ ይዞ የሚያድግና ለሁሉም እኩል ዕድል የሚሰጥ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዴት መገንባት ይቻላል ለሚለው የአንዳንድ ሀገሮች ተሞክሮ የሚያሳየው ከዴሞክራሲ በኋላ ይመጣል በሚል ጨፍልቀው የያዙ መኖራቸውንም ዶክተር እዮብ አስታውሰዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ብዝኃነት ባለበት ግን የሚታሰብ እንዳልሆነ የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው የሚያግባባና አንድ የሚያደርግ ያለቀለት ፖለቲካ ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር እዮብ ገለጻ፤ ለየብቻ መቆም ሳይሆን በጋራ ጉልበታችንን አንድ ላይ ስናደርግ ብዙ ርቀት መሄድ እንችላለን የሚል እሳቤ መያዝ ያስፈልጋል። መንግሥታት በኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው እንቅስቃሴ መንግሥት ኢኮኖሚው ውስጥ ሁሉን ነገር እሠራለሁ ብሎ የገባበት ነበር። ይህም በመንግሥትና በግል ዘርፉ መካከል አለመተማመንን ፈጥሮ ቆይቷል ሲሉም አስረድተዋል።

አሁን ባለው የለውጥ መንግሥት የግሉ ዘርፍ የሚገባውን ሚና መጫወት እንዳለበት የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ መንግሥት አቅጣጫ የመስጠትና አዲስ ሀሳብ የማፍለቅ ሚና የመወጣት ድርሻ ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑንም አመልክተዋል።

መንግሥት የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ ሲጀምር የመሪነት አቅጣጫውን እያሳየ መሆኑን ዶክተር እዮብ ጠቁመው፤ ከፈንታሌ እስከ ኤርታሌ የሚለው ፕሮጀክት በተለይም አዋሽ ውስጥ የሚከናወነው ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ዕድል የሚያመነጭ ሥራ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ዶክተር እዮብ እንዳሉት ይሄ ተግባር የሀገር አቅም እንዴት ማደግ እንዳለበት ነው የሚያሳየው። ፖለቲካል ኢኮኖሚው ለሁሉም በሚጠቅም መልኩ መሆን አለበት፣ የተንሸዋረረ አመለካከት መቀየር አለበት፣ ሁሉም አንድ ላይ ካልሆነ ወይንም ካልተደመረ መሻገር አይቻልም።

የግሉ ዘርፍ ሚና ከፍተኛ ነው ሲባል መንግሥት ቁጭ ብሎ ይጠብቃል ማለት እንዳልሆነና ይልቁንም ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ዶክተር እዮብ ተናግረዋል።

# ከበልግና መኸር ግብርና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሬቱ ለቀጣይ የምርት ሂደት እንዲዘጋጅ ይደረጋል ሲሉ ገልጸዋል።

በደጋማው የዞኑ አካባቢዎች ደግሞ ለመኸር ግብርናው 261 ሺህ 392 ሔክታር መሬት ለማልማት አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን ጠቁመው፤ ከዚህ ውስጥ በ181 ሺህ በላይ ሔክታር መሬቱ ላይ ስንዴ በክላስተር እንደሚለማ ተናግረዋል።

ለመኸር ግብርና ዝግጅት ከሚደረግበት አጠቃላይ መሬት 50 በመቶ በሜካናይዜሽን በተደገፈ አሠራር እንደሚታገዝ አቶ አሊዬ ተናግረዋል።

አገራችን ከውጭ የምታስገባውን የስንዴ ምርት በአገር ውስጥ ለመተካት በሚደረገው ጥረት የባሌ ዞን የሚጠበቅበትን ሚና እየተወጣ ነው ያሉት የቢሮው ኃላፊ፤ በዚህም የግብርና ሥራ የሚከናወንባቸው 190 ቀበሌዎች አስፈላጊው የግብርና ሥራ እንዲከናወን እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በዞኑ በአጠቃላይ ለበልግና መኸር የግብርና ልማት ከ509 ሺህ 303 ሔክታር በላይ መሬት ጥቅም ላይ ውሏል። ከዚህ ውስጥ 335 ሺህ ሔክታር መሬቱ ለስንዴ ምርት የዋለ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በ2014 ዓ.ም 18 ሺህ 519 ሔክታር መሬት ላይ የመስኖ ስንዴ ለምቷል።

አቶ አሊዬ እንዳስታወቁት፤ ባሌ ዞን የተለያየ አግሮ ኢኮሎጂ ያለው አካባቢ ነው። ዞኑ ካሉት 11 ወረዳዎች መካከል ስድስቱ ወረዳዎች በመሬት አቀማመጣቸው ከፍተኛ ቦታ ላይ ሲገኙ፤ የተቀሩት አምስት ወረዳዎች ደግሞ ዝቅተኛ ቦታ ላይ ይገኛሉ። በዚህ የተነዛ በዞኑ የተለያዩ የግብርና ልማት ሥራዎች ይከናወናሉ።

በተለይም የቢራ ገብስ፤ ማሾ ፣ ቡና፣ የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎች እንዲሁም የቅባት እህሎችን ይመረታሉ ሲሉ ኃላፊው አስረድተዋል።

ለምርት የሚረዱ የተለያዩ የምርጥ ዘር፤ የበሽታ መከላከያ ኬሚካሎችና ማዳበሪያ አቅርቦት በተሻለ ሁኔታ ለማቅረብ ቢሮው የግብርና ባለሙያዎቹን አሰማርቶ በየጊዜው ክትትል እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

እንደ አቶ አሊዬ ገለጻ፤ ለግብርና ግብዓት አቅርቦቱ ውጤታማነት ከዘር ብዜትና ምርምር ተቋማት፤ ከኅብረት ሥራ ማኅበራት ፣ ከአርሶ አደሮችና ከግሉ ዘርፍ የግብርና ተሳታፊ አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ ይገኛል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያውያን ሽብርተኝነትን የሚታገሱበት ስብዕና የላቸውም!

የምስራቅ አፍሪካ በዓለም ላይ ያልተረጋጉ ከሚባሉትና ለሽብርተኞች መፈልፈያነት ምቹ ስፍራዎች ናቸው ተብለው ከሚታወቁት አካባቢዎች አንዱ ነው። ኢትዮጵያ የምትገኝበት አካባቢያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ለሽብርተኝነት ተጋላጭ ቢያደርጋትም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ሽብርተኞችን እንደ አመጣጣቸው እያሳፈሩ ሲመልሱ ቆይተዋል። በዚህ አኩሪ ተግባራቸውም በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ ከበሬታን ተጎናጽፈዋል።

አጎራባች ሶማሊያን ሲመራ የቆየው የዚያድ ባሬ መንግሥት ከወደቀ በኋላ ሀገሪቱ ለረጅም ዘመን ያህል መንግሥት አልባ ሆና መቆየቷ ሶማሊያ የሽብርተኞች መናኸርያ እንድትሆን አድርጓታል። ይህንንም ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የኢትዮጵያን ሰላምና ዕድገት የማይሹ ወገኖች ሽብርተኞችን አስርጎ በማስገባት ሀገሪቱን የደም ምድር ለማድረግ ቢሞክሩም የሽብርተኞቹ እኩይ ሴራ በኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይሎች በየጊዜው ሲመክን ቆይቷል። አሁንም እየመከነ ይገኛል። ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባና በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ታቅደው የከሸፉ የአልሸባብ የሽብር ተግባራት ይህ የሽብር ቡድን ኢትዮጵያን ለማተራመስና ለመጉዳት ምን ያህል እንቅልፍ አጥቶ እየሠራ መሆኑን አመላካች ነው።

ኢትዮጵያ ሽብርተኝነትን የመዋጋትና ብሎም የማንበርከክ አኩሪ ታሪክ አላት። በሶማሊያ ውስጥ የሚርመሰመሰውን የአልሻባብ ኃይል ለማስወገድ ሠራዊቷን ከሁሉ ቀድማ በሶማሊያ ያሰማራችው ኢትዮጵያም ነች። የኢትዮጵያ ሠራዊትም ሶማሊያ ከገባ ጀምሮ አልሻባብ እየተዳከመ በመምጣቱ የሶማሊያ ሕዝብ አንጻራዊ ሰላም እንዲጎናጸፍ አስችሏል። በዚህ አኩሪ ተግባሯም ኢትዮጵያ የቡድኑ ቀዳሚ ዒላማዎች ከሆኑት ሀገራት መካከል አንዷ ብትሆንም፣ ምስጋና ለኢትዮጵያ የደህንነትና የጸጥታ ተቋማት ይሁንና እስካሁን ድረስ ከሙከራ የዘለለ ይህ ነው የሚባል ጥቃትን ለመፈጸም አልቻለም። ከጸጥታና ደህንነት ኃይሎች የተሳካ ሥራ ጀርባ ሕዝቡ ሽብርተኝነትን በመጠየፍና በማጋለጥ በኩል እያደረገ ያለው አኩሪ ድጋፍ የአልሸባብን የጥፋት ዕቅድ ለማምከን ትልቅ አቅም ሆኗል።

በውስጥ የሰላም መደፍረስና መከፋፈል አለ ከሚል የተሳሳተ እሳቤ በመነሳትም ሰሞኑንም የአልሻባብ ኃይል በሶማሌ ክልል በኩል ሾልኮ በመግባትና ከሽብርተኛው ኦነግ ሸኔ ጋር በመግጠም ሀገሪቱን የሽብር ማዕከል ለማድረግ ሙከራ ቢያደርግም በሶማሌ ክልል ልዩ ኃይልና በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የተቀናጀ ሥራ ቡድኑ አሳፋሪ ሽንፈትን ተከናንቦ ለወሬ ነጋሪ ሳይተርፍ በሙሉ ተደምስሷል። ሽብርተኛውን ኃይል ለማስወገድ የኢትዮጵያ ጸጥታ ኃይሎች በከፍተኛ ብስለትና ጽናት በወሰዱት የተቀናጀ ርምጃ የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች በጀግናው መከላከያ ሰራዊታችን ተገድለዋል። በተጨማሪም ከ200 በላይ የሚሆኑት የቡድኑ አባላት ከመገደላቸውም በላይ ቡድኑ ይዟቸው የመጣቸው 13 ተሽከርካሪዎቹ ወድመውበታል፤ ትጥቅና ስንቁም ተማርኮበታል።

የኢትዮጵያን ሰላምና ዕድገት የማይመኙ ጎረቤት ሀገራት በውስጥ ካሉ ባንዳዎች ጋር በመሆን ሀገሪቱን ለማመስ ዘወትር የሴራ ገመድ ሲገምዱ ይኖራሉ። የኢትዮጵያን መፈራረስ ዘወትር የሚያልመው አሸባሪው ሕወሓት ከአሸባሪው ሸኔ ጋር በማበርና አልሻባብን የጥፋት አጋራቸው በማድረግ በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ዕልቂት አቅደው የነበረ ቢሆንም በጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችንና በሶማሌ ልዩ ኃይል ተመክቶ አሳፋሪ ሽንፈት ተከናንቧል። በዚህም ኢትዮጵያውያን ሽብርተኝነትን የሚቀበል አዕምሮና የሚሸከም ትከሻ እንደሌላቸው ለሽብርተኞች የማያዳግም ትምህርት ሰጥተዋል።

የሰው ሕይወት መቅጠፍና ማውደም መለያው የሆነው አሸባሪው አልሻባብ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች በተለይም በምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ዋናው የደም መፋሰስና የሞት ምንጭ ነው። ቡድኑ ከአልቃኢዳ ጋር ባለው ኅብረትም ለቀጣናው ብቻም ሳይሆን ለዓለም ሰላምና ደኅንነት ዋና ሥጋት ከሚባሉ ሽብር ቡድኖች አንዱ ነው። ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ለበርካታ ዓመታት ይህንን የሽብር ቡድን በገባበት እየገቡ የሽብር ውጥኑን ሲያመክኑ ቆይተዋል። በአዲስ አበባ ውስጥ የሽብር ጥቃት ለመፈጸም አቅደው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ በርካታ የሽብር ቡድኑ አባላት በኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውም የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

ኢትዮጵያውያን በውስጥና በውጭ የሚገኙትን የሽብር ቡድኖች እየደመሰሱ ልማታቸውን በማፋጠን ላይ ይገኛሉ። ለአፍታም በሽብርተኝነት ላይ አንቀላፍተው የማያውቁት ኢትዮጵያውያን የዓለም ሰላም ስጋት በሆነው አልሻባብና ግብረ አበሮቹ ሕወሓትና ሸኔ ላይ እየወሰዱት ያሉትን የጸረ ሽብር ዘመቻ ከዳር የሚያደርሱበት ቀን ሩቅ አይሆንም!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# ሕዝብና መንግሥትን «ሆድና ጀርባ» የማድረጉ ሴራ

**ሜላት ኢያሱ**

ጠላት ኢትዮጵያን የማፈራረስ አጀንዳ ይዞ ሲነሳ የመጀመሪያ ተግባሩ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ወይም ሕዝብ ከመንግሥት ጋር ያለውን ጠንካራ መስተጋብር መናድ፣ አንድነቱን ማጥፋት ነው። ይህን ካደረገ ያሰበውን ሁሉ ለማሳካት መንገዶች ሁሉ አልጋ በአልጋ ይሆኑለታል። በዚሁ ስሌቱ መሰረት ሕዝብ በመንግሥት ላይ አመኔታ እንዳይኖረውና እርስ በእርሱም እንዳይተማመን የሚያደርጉ በርካታ ሴራዎችን እየጎነጎነ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ያለውን መንግሥት ለማስጠላት ብዙ ርቀት ሄዷል።

ዛሬ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች እኩይ ተግባር በፈጸሙ ቁጥር የጠላትን ተለዋዋጭ ባህሪ የመረዳት ክፍተት ያለብን አንዳንድ ሰዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ጉዳዩን ከማይመለከተው ማህበረሰብ ጋር ወይም ከመንግሥት ጋር እያስተሳሰርን እንኮንናለን። ይህ አለመረዳታችን ታዲያ ወትሮም ኢትዮጵያ እንድትበታተንና እንድተፈራርስ ለሚፈልጉት ጠላቶቻችን ምቹ ሁኔታ ስለፈጠረላቸው በየጊዜው ቦታና አጀንዳ እየቀያየሩ ማህበራዊ አንድነታችንን እንዲያናጉት እድል እየሰጣቸው ይገኛል።

ያልተማርንና ስለፖለቲካ ምንም አይነት ግንዛቤ የሌለን ሰዎች ብቻ ሳንሆን ሕዝብን ወክለው በምክር ቤት ወንበር ላይ የተቀመጡ ሰዎች ሳይቀሩ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ጸረ ሰላም ሃይሎች የሚፈጽሙትን የንጹሓን ጭፍጨፋ የመንግሥት ባለስልጣናት እንዳስደረጉት አድርጎ የመውሰድ አዝማሚያም ይስተዋላል። እንዲህ አይነቱ በበቂ ማስረጃ ያልተረጋገጠ አሉባልታ ደግሞ በሕዝብና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሻክር ከማድረግና የጠላትን ዓላማ ከማሳካት ባሻገር ፋይዳ አይኖረውም። ይልቁንም ህብረታችንን ያፈርሳል፤ ተሰባስበን ጠላቶቻችንን እንዳን መከት አቅም ያሳጣናል።

በእርግጥ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ እየሠሩ ከጸረ ሰላም ሃይሎች ጋር በመመሳጠር የመንግሥትን አቅም ለማዳከም የሚዶልቱ፤ የጠላትን ተልእኮ ተቀብለው ደፋ ቀና የሚሉ ጥቅመኞች የሉም ማለታችን አይደለም።አሉ። በመንግሥት ጉያ ስር ተሸጉጠው መዋቅሩን ለማዳከም ወይም ሕዝብና መንግሥትን የማለያየት ተልእኮ ተቀብለው በኅቡዕ የሚንቀሳቀሱ ጸረ ሕዝቦች በየተቋሙ መሰግሰጋቸው ለማንም ግልጽ ነው።

ከዚህ የምንረዳው ኢትዮጵያን የማፈራረስ አጀንዳ ያነገቡትና መንግሥትን እየተገዳደሩ ያሉት የውጭ ሃይሎችና በይፋ የትጥቅ ትግል እያደረጉ ያሉት ብቻ አለመሆናቸውን ነው። እነዚህ በመንግሥት እቅፍ ውስጥ ያሉ የጭቃ ውስጥ እሾኾች በማር የተሸፈነ ውጫዊ ማንነት ይዘው ውስጣቸው ግን መርዝ ነው፤ እግራቸውን በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ተክለው የዚያኛውን ወገን ፍላጎት ያስፈጽማሉ፤ ከጎናችን የቆሙ ሲመስለን ከኋላችን ይገኛሉ፤ የኢትዮጵያን ሰላምና ብልጽግና ለማረጋገጥ ብዙኋኑ የሚያደርገውን ትግልና የልማት ግስጋሴ ወደ ፊት ይገፋሉ ሲባል ወደ ኋላ ይጎትታሉ። እነዚህን በየቢሮው የተሰገሰጉ አስመሳዮች የትጥቅ ትግል እናደርጋለን እያሉ ንጹሓን ወገኖቻችንን ከሚጨፈጭፉትና ለብዙዎች መፈናቀልና ለሃብት ውድመት ምክንያት ከሆኑት ጠላቶቻችን ነጥለን ልንመለከታቸው አይገባም።

እነዚህ ጥቅመኞች ከመቶ ሚሊዮን በላይ የሆነውን ሰላም ወዳድ ሕዝብን አሸንፈው መውጣት ይችላሉ ባይባልም፤ ለጊዜውም ቢሆን የመንግሥትን እልፍኝና ጓዳ ተቆጣጥረው መልካቸውን እንደ እስስት እየቀያየሩ በሚፈጽሙት ደባ ሀገርና ሕዝብን ማወካቸው አይቀርምና አደብ እንዲገዙ ማድረግ ያስፈልጋል።

የነዚህ አስመሳዮች ተለዋዋጭ ባህሪ ከእስስት ተፈጥሮ ጋር በከፊል ይዛመዳል። እስስት በተፈጥሮ ምግቧን ለማደን ስትል መልኳን ትቀያይራለች። ቅጠል ላይ አረንጓዴ፤ አፈር ላይ ግራጫ ሆና እያደነች ሕይወቷን ታኖራለች። ከዚህ አንጻር በኅቡዕ የሚንቀሳቀሱ ጸረ ሰላም ሃይሎች አስመስሎ የመኖር ባህሪያቸው ከእስስት ተፈጥሮ ጋር የሚመሳሰል ነው። እስስት እራሷን ከቅጠል ጋር አመሳስላ የምትፈልጋቸውን ነፍሳት እንደምታጠቃ ሁሉ እነርሱም እራሳቸውን ከሕዝብና ከመንግሥት ጋር አመሳስለው የፈለጉትን አካል ያጠቃሉ።

ከሰሞኑ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ጥቂት ግለሰቦች የፈጸሙት መጥፎ ድርጊት መነጋገሪያ እንደነበር የሚታወስ ነው። በተለይም ሀገራችንን ካለችበት ችግር ለማውጣት ብዙኃኑ ኢትዮጵያዊ ርብርብ በሚያደረግበት በዚህ ወቅት የተሰጣቸውን ከፍተኛ የመንግሥት ሃላፊነትና የሕዝብ አደራ አሽቀንጥረው በመጣል ሀገርን ያስኮረፈ ጸያፍ ሥራ መሥራታቸው ጉዳዩን የከፋ አድርጎታል።

እንዲህ አይነቱ ፍላጎትና ድርጊት ሕዝብን በመንግሥት ላይ ለማሳመጽና የመንግሥትን መዋቅር ለማዳከም ያለመ ይመስላል። በጦርነት ምክንያት ተፈናቅለው ለምግብና ለመጠለያ ችግር የተጋለጡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን እጃቸውን ዘርግተው የመንግስትና የወገን ያለህ በሚሉበት በዚህ አንገብጋቢ ሰዓት በስማቸው የተመጸወተውን ርዳታ ሽጦ ለግል ጥቅም የሚያውል የመንግሥት ሃላፊን ተመልክቶ ጉዳዩን ከተራ ሌብነት ጋር ብቻ ማያያዝ የዋህነት ነው። የዚህ አይነቱ ስርቆት ዓላማ የራስን ጥቅም ከማስጠበቅ ባለፈ ፖለቲካዊ አሻጥር ያለበት ለመሆኑ መጠራጠር አያስፈልግም። ያ ባይሆን ኖሮ ሀገር በፈተና ውስጥ እያለች ለተረጂዎች የተሰፈረውን ቀለብ ሽጦ ለግል ጥቅም ማዋል ባልተገባ ነበር።

የዚህ አይነቱ ሴራ ዓላማ ችግርን ማባባስና የተረጂዎችን መከራ ድምጽ ከፍ ማድረግ፣ ከዚያም መንግሥትን ጫና ውስጥ ማስገባት፤ መንግሥት አፋጣኝ ምላሽ አልሰጠም ተብሎም ሕዝብ በመንግሥት ላይ ትችትና ተቃውሞ እንዲያነሳ ማድረግ ፤ ቀጥሎም ለሕዝብ ችግር የማይደርስ ግድ የሌለውና አቅመ ደካማ የሆነ መንግሥት ተደርጎ እንዲታይ ማደረግ ነው። እንግዲህ ለዚህ ነው የአደጋ ስጋትና ችግርን ይፈታል ተብሎ የተቋቋመው ‹‹ብሄራዊ የአደጋ ስጋትና ሥራ አመራር ኮሚሽን›› አደጋ መፍታቱን ትቶ አደጋ ፈጣሪ የሆነው። ይህ ሲባል ግን ችግሩ የተቋሙ ነው ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ተቋሙን ሲመሩ የነበሩትን የበላይ አመራር ማለት እንጂ።

በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ከተማ ኮንዶሚኒየም ቤቶች እጣ አወጣጥ ላይ የተፈጸመው ማጭበርበርም ከዚሁ ጋር የሚዛመድ ነው። ጥፋቱን የፈጸሙት ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች እንጂ መንግሥት አይደለም። መንግሥት ቢሆንማ ኖሮ የእጣውን መጭበርበርና መሰረዝ ይፋ አድርጎ ዳግም ትክክለኛ እጣ ለማካሄድ ባልተዘጋጀ ነበር። ይልቅስ እንዲህ አይነቱ ጉዳይ መንግሥት ከታጠቁ ሃይሎች ጋር ብቻ ሳይሆን በጉያው ከተሰገሰጉት ከሃዲዎች ጋርም እየታገለ ስለመሆኑ አንድ ማሳያ ሊሆን በተገባ ነበር። ጠላት አስርጎ ባስገባቸው አባላቱ የመንግሥትን አሠራር ለማበላሸትና መዋቅሩን ለማዳከም የሚደርገውን ሴራ እየተመለከትን ከመንግሥት ጎን ቆመን መታገል ሲገባን መንግሥትንና በጉዳዩ እጃቸው የሌለበትን የመንግሥት አመራሮች እየተቸን የጠላት አጀንዳ አስፈጻሚዎች ልንሆን አይገባም።

ምክንያቱም አጥፊዎቹ ምንም እንኳን በመንግሥት ተቋማት ውስጥ በሃላፊነት ተመድበው የሚሠሩ ቢሆንም ግለሰቦች እንደመሆናቸው፤ የግለሰቦችን የተበላሸ አስተሳሰብና አሠራር የመንግሥት ጥፋት አድርጎ መመልከት ተገቢ አይሆንም። ካለንበት የሽግግር ወቅት አንጻር የተለያየ ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች በየተቋማቱ መኖራቸውን መርሳት አያስፈልግም። የሚመለከተው አካል ተቋማትን እየፈተሸ ተገቢ ሰዎችን በተገቢው ቦታ የማስቀመጥ ሃላፊነቱን ግን መወጣት ይኖርበታል። መንግሥት ሥራውን ይሥራ፤ እኛም እናግዘው፤ ያን ጊዜ ሰላማችንን እና እድገታችንን ማረጋገጥ እንችላለን። ከዚያ ውጭ ግን በየቢሮው ከጠላት በተሰጣቸው ተልእኮ መሰረት ሕዝብና መንግሥትን ለማለያየት የሚሰሩ አካላት በተጋለጡ ቁጥር መንግሥትን ተባባሪና ደጋፊ ማድረጋችን ወይም በጉዳዩ የሌሉ ሹመኞችን መውቀሳችን ‹‹ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ›› ይሆንብናል። ከዚህም በላይ ጠላት በቀደደልን ቦይ ሰተት ብለን እየፈሰስን መሆኑን በማወቅ በጉዟችን ሁሉ ምክንያታዊ እንሁን።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# «በ11 ወራት ውስጥ ከተያዘው 581 ሀሰተኛ ሰነድ መካከል 411ዱ መታወቂያ ነው»

አቶ ሙሉቀን አማረ
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር



ፎቶ-አዩብ ተፈሪ

አስመረት ብስራት

**የሰው ልጅ በመኖር ሂደት ውስጥ ሀብት ማፍራቱ የተለመደ ነው። የሀብት ባለቤትነቱን ደግሞ ህጋዊ ለማድረግ ህጋዊ ሰነድ የሚያገኝበት ተቋም ያስፈልገዋል። ሀብትን በአግባቡ ለማስተዳደር ከባለቤትነት መብት ጀምሮ የተለያዩ 51 አይነት አገልግሎቶችን የሚሰጠው ተቋም የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት በመባል ይታወቃል።**

**ከተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ከአቶ ሙሉቀን አማረ ጋር በተቋሙ ስለሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፤ በተለይ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ እያጋጠመ ስላለው ችግርና (ሀሰተኛ መረጃ)፣ ሙስናን የሚመለከት እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ቃለመጠይቅ አድርገናል። ከእርሳቸው ጋር የነበረንን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል፡፡**

**አዲስ ዘመን፤ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት አሁን ያለበት ቁመና ምን ይመስላል?**

**አቶ ሙሉቀን፡-** የሰነዶች ማረጋገጫ የፌዴራል ተቋም ነው። ተቋሙ ሰነድ የማረጋገጥና የምዝገባ አገልግሎት የሚሰጥበት ነው። ተቋሙ አገልግሎት የሚሰጠው በፌደራል ደረጃ ነው ሲባል አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ ላይ ከትሞ የሚሰራ ተቋም ነው። በተመሳሳይ ይህን አገልግሎት በተቀሩት ክልሎች የሚሰጡት የፍትህ ቢሮዎች ናቸው። ሰነድ የማረጋገጥና የምዝገባ አገልግሎት ሲባል በርካታ አገልግሎቶችን በውስጡ ያየዘ ነው። በቁጥር ይህ ነው ባይባልም ዋናው ከሀገሪቱ ሕግ ጋር የማይጣረስ ካለን ሀገራዊ ሞራል ጋር የተጣጣመ ሰነድ የማረጋገጥ አገልግሎት ይሰጣል።

እስካሁን ባለው ሂደት ወደ 51 አይነት አገልግሎቶች ወደ ተቋሙ ሰነድ ይረጋገጠልኝ ሲሉ ይመጣሉ። በቀጣይም ይረጋገጥልኝ የሚባል ሰነድ ቢመጣ የሀገሪቱን ሕግና ሞራል ከጠበቀ ይስተናገዳል። ከ51ዱ አይነት አገልገሎቶች ውስጥ ደግሞ አብዛኛው የውክልና አገልግሎቶች፣ የንብረት ማስተላለፍ ውሎች፣ የኪራይና የብድር ውል እንዲሁም የኩባንያዎች መመስረቻና ማሻሻያ ቃለ ጉባኤዎች ሰፊውን ስፍራ ይይዛሉ።

አሁን ባለው ሁኔታ ተቋሙ በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት እየሰጠ በአዲስ አበባ አስራ አራት ቅርንጫፍ በድሬዳዋ ያለውን አንድ ጨምሮ በድምሩ አስራ አምስት ቅርንጫፍ ያለው፤ በኦንላይንም ጭምር እየታገዘ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ተቋም ነው። ተቋሙ ከባንኮችና ከመሳሰሉት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቴክኖሎጂ በመተሳሰር እየሰራ ነው። በሁሉም ቅርንጫፎች በድምሩ በቀን እስከ 6 ሺህ 700 ተገልጋዮችን እያስተናገደ ሲሆን፣ ይህም በአማካይ የተቀመጠ የተገልጋይ መጠን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል ተቋሙ በተለያዩ ጊዜዎች ተሸላሚ ነበር፤ ይህ የስራ ጥንካሬ ግን ለአንድ ሰሞን ነው ወይስ በትክክል የአሰራር ስርአቱን ጠብቆ የህዝብ እርካታውን ይዞ እየሄደ ነው ?**

**አቶ ሙሉቀን፡-** ይህ ተቋም በአስራ ዘጠኝ ዘጠናዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በቀን ሰላሳ ሰው የሚያስተናግድ አቅም ነበረው ። አሁን ደግሞ ወደ 6 ሺ 700 ከፍ ብለናል። ይህ ቁጥር ግን በአንድ ጊዜ የተደረሰበት ሳይሆን በሂደት መጥራት ያለባቸው አሰራሮች እየጠሩ፤ የተለያዩ ደረጃዎችን እያለፈ ነው እዚህ ደረጃ የደረሰው። ተቋሙ ቀደም ሲል በአገልግሎት አሰጣጡ በርካታ ቅሬታዎችን የሚያስተናግድ ተደራሽ ያልነበረ በአንድ ማእከል አገልገሎት ይሰጥ የነበረ ነው ። በ2001 ዓ.ም አካባቢ ተቋሙ በሰራው ሪፎርም በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ጥራት ስራ ድርጅት ተወዳድሮ ተሸላሚ ሆኗል።

ከሽልማቱ በኋላ ግን ስራ ማቆም ሳይሆን ተደማሪ ለውጦችን ለማምጣት እየተጋ ይገኛል። አዳዲስ ስራዎችን መስራት፤ ተጨማሪ የአገልግሎት ክፍተቶችን በመመልከት ማሻሻያዎችን እየሰራ ይገኛል። የኦንላይን አገልግሎቶች፣ ቅርጫፎችን የማስፋት ስራ፣ የህዝቡን ፍላጎት በማየት አገልግሎት ብዛትን መጨመርና ሌሎች ስራ እየተሰሩም ይገኛሉ። ከነበረው ላይ ወደኋላ መመለስ ሳይሆን ወደፊት እየተጨመረ የተገልጋይን እርካታ ለመጨመር በትጋት ወደ ከፍታ ግስጋሴውን ቀጥሏል።

**አዲስ ዘመን፡- ከየሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት በአብዛኛው ከንብረት ጋር የተያየዙ ስራዎችን ይሰራል፤ በዚህም በርካታ ህገወጥ ሰነዶች ሊቀርቡ ይችላሉ፤ ይሄ እንዴት ይስያል? ከፍትህ አካላት ጋርስ በቅርበት የመስራቱ ጉዳይ ምን ይመስላል?**

**አቶ ሙሉቀን፡-** አንድ ሰው ሰነድ ሊያረጋግጥ ሲመጣ ዋነኛው የሚጠበቅበት ነገር መታወቂያ ይዞ መምጣት ነው። ለሁሉም አገልግሎቶች የሚጠየቀው የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ነው። በዚህም ከመታወቂያ ጋር ተያይዞ የሚደረጉ ማጭበርበሮች ለተቋማችን ከፍተኛ ፈተና የሆነ ጉዳይ ነው። ከመታወቂያው በተጨማሪ የጋብቻና ያላገባ መረጃዎች እንዲሁ በሃሰተኛ ሰነድ ከሚቀርቡት ማስረጃዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

እነዚህ ሰነዶች ለማጭበርበር ተጋላጭ የሆኑበት ምክንያትም ንብረት የማስተላለፍ ተግባር ላይ ባለትዳር ከሆነ የትዳር አጋሩን ይሁንታ የሚጠይቅ፤ ባለትዳር ካልሆነ ደግሞ ያላገባ መሆኑን ማስረጃ ማምጣት ይኖርበታል። ብዙ ሰዎች ከትዳር አጋር ለመሸሽ ወይም የትዳር አጋርን እውቅና ላለመስጠት ሲሉ ያላገባ ማስረጃ በሀሰት ያዘጋጃሉ።

ያላገባ ማስረጃና መታወቂያ ለተቋሙ ከፍተኛ ፈተና እየሆነበት ያለ ችግር ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በቁጥር ለመግለፅ ያህል ባለፈው በጀት አመት ከሀምሌ 2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ 581 ሀሰተኛ ሰነድን ለመያዝ ተችሏል። ከ581 ሃሰተኛ ሰነዶች መካከል 411ዱ መታወቂያ ነው። በሀሰተኛ መታወቂያ በአብዛኛው ለውክልና አገልግሎት ነው የሚውለው። በዚህም ከባንክ ገንዘብ ማውጣት ሊሆን ይችላል። የሰው ንብረት መሸጥ ሊሆን ይችላል፤ ይህ ሁሉ ወንጀል ይሰራበታል።

ከባንክ ጋር ለሚፈጠሩ ችግሮች ሙሉ ለሙሉ ዘግተናል። አንድ ሰው ውክልና ሲሰጥ ፎቶ ይነሳል፤ የያዘው መታወቂያም ይያያዛል፤ ሲኩሪቲ ኮድም አብሮ ይኖራል፡፡ በዚህም ሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ሁሉም ባንኮች የዚህን ተቋም የመረጃ ቋት መመለከት ይችላሉ። በውክልና ገንዘብ ማውጣት ሲፈለግ ውክልናው ከዚህ ተቋም መገኘቱን ያረጋግጣሉ። ይሄ የባንኮችን መጭበርበር ቀንሷል።

እንደ ባንኮቹ ሁሉ የተሽከርካሪ ሽያጭ ስም ከሚያዞረው ተቋም ጋር ተቋማችን ተሳስሯል። የአዲስ አበባ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፍቃድ ጋር ባለው ትስስር ያለውን ሽያጭ ውልና ውክልናን መመልከት ይችላል።

ሌላው ማጭበርበርን ለመከላከል ሁሉም ህዝብ ውክልና ወቅት ላይ ያለውን ኪዋር ኮድ በሞባይል አፕሊኬሽን ኪዋር ኮዱን በማንበብ እራሱን ከመጭበርበር መጠበቅ ይችላል።

በአጠቃላይ ተቋሙ ያለው ስልጣን የያዛቸውን ሀሰተኛ ሰነዶች በቀጥታ ለፖሊስ በማስረከብ ተጠያቂ እንዲሆን እስከማድረግ ድረስ ብቻ ነው። ይሄ ለያዝነው ሀሰተኛ መረጃ ነው፤ ያልያዝነውም ሊኖር ይችላል። ተይዘው ወደ ፖሊስ የቀረቡት በጥፋታቸው ልክ እየተቀጡ ስለመሆኑ ጥናት ቢጠየቅም በተሰራው ልክ ግን እየተቀጡ አለመሆኑ እየታየ ነው። የፍትህ አካላት ግን ይህን ሀሰተኛ ሰነድ ይዘው የሚገኙ አጥፊዎች እንዳይበረከቱ ቅጣቱ ላይ ትኩረት ቢያደርጉ የተሻለ ውጤት ይመጣል ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- አንድ ተገልጋይ ወደ ተቋሙ ሲመጣ መብትና ግዴታውን ያውቃል? እናንተስ አገልግሎት መስጠት ግዴታችሁ መሆኑን ታውቃላችሁ? በእጅ መንሻ አገልግሎት የሚፈልጉ ተገልጋዮች ካሉስ እንዴት ነው ይሄንን የምትከላከሉት?**

**አቶ ሙሉቀን፡-** እውነት ለመናገር ማህበረሰቡ ተገቢ አገልግሎት አገኝበታለሁ ብሎ በልበ ሙሉነት ከሚመጣበት ተቋም አንዱ ይህ ተቋም ነው። ለዚህም መረጃው ተደራሽ መሆኑና በተቋሙ ሄዶ መገልገል መብቱ እንደሆነ የሚያዉቅበት መሆኑ በራሱ ማህበረሰቡ በተቋሙ እምነት አሳድሯል።

በዚህ ተቋም ለነገ የሚባል ስራ አለመኖሩንም ተገልጋዩ ያውቃል፤ እንኳን ለቀጣዩ ቀን ሊቀጠር ቀርቶ ጠዋት መጥቶ ከሰዓት ተመለስ ቢባል ፍቃደኛ አይደለም። ሌላው እዚህ ተቋም ላይ አገልግሎት እየሰጠ ያለ አንድ የተቋሙ ሰራተኛ አላገለግልም ቢል ተገልጋዩ የት መሄድ እንዳለበት ያውቃል። አቤቱታውን ተቀብሎ የሚያስተናግደው ሰው በቦታው በመኖሩ ሁሉም በር ለተገልጋዩ ክፍት ነው። ይህም በሁሉም የስራ ቀን ባለጉዳዩ ቅሬታውን ማቅረብ በራሱ የመረጃ አለመሟላት አገልግሎት ሳያገኝ ካልሄደ በስተቀር ማንም ተገልጋይ ሳይገለገል ወደቤቱ አይመለስም።

ሌላው በማንኛውም ሰዓት ኃላፊዎች ዘንድ ቢደወል የስልክ ጥሪውን የማይመልስ የለም፤ ባለጉዳይ ሲደውልም ሲያመለክትም ወዲያው እርምጃ ይወሰዳል። ለዚህም ማስረጃ እናንተ ናችሁ። በደወላችሁበት ቅፅበት ስልካችሁን መልሰናል። ከዚህ አልፎ ያልተገባ ተግባር የሚያከናውን ባለሙያ ቢገኝ ተገቢውን ቅጣት ይቀጣል። ይህ ሲባል ይህንን ተግባር የፈፀመ ባለሙያ በስራው ላይ ብናቆየው ስራው ላይ አደጋ ያመጣል ተብሎ ሲታሰብ በቀጥታ ከስራው ታግዶ የማጣራት ስራ ይሰራል። ለምሳሌ አንድ ሙስና ተጠየቅኩኝ የሚል ተገልጋይ አመልክቶ እያለ ማስረጃ አቅርቦ እያለ ያንን ባለሙያ መቀመጫው ላይ ማየት ተገቢ አይሆንምና ታግዶ የማጣራት ስራ ይሰራል። በዚህም አካሄድ እስከ አስራ ሁለት ባለሙያዎች በዲሲፕሊን የተቀጡም አሉ።

ተገልጋዮች ከሚሰጡት ጥቆማ በተጨማሪ በደህንነት(በሲኩሪቲ) ካሜራ ክትትል የሚደረግ ሲሆን፣ በዚህም እጅ ከፍንጅ የመያዝ ስራ ይሰራል። በካሜራው አገልግሎት አሰጣጥ ላይ መቀዛቀዝ ሲኖር፣ የማንቃት ክፍተት ሲኖር የመሙላት ስራም ተቋሙ በቀዳሚነት የሚያከናውነው ተግባር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በስራ ሂደት ውስጥ ተቋሙ የሚያጋጥመው ትልቅ ፈተና ምንድን ነው?**

**አቶ ሙሉቀን**፡- አስቀድሜ እንደገለጽኩት የተቋሙ ትልቁ ፈተና ሀሰተኛ ሰነድ ነው። በዚህ ተቋም እያጋጠመ ያለ ወደ ፊትም እያጋጠመ የሚቀጥል ይመስለኛል። በተለይ ከሀሰተኛ ሰነዶች ትልቁን ድርሻ የሚይዘው መታወቂያና ያለገባ ማስረጃ ነው። መታወቂያ የሚሰጠው አካል ማለትም ወሳኝ ኩነት ጋር በትብብር እየሰራን ቢሆንም የዜጎች የሁሉም መረጃ ዳታ ላይ አለመኖሩ ትንሽ ፈታኝ አድርጎታል።

ሌላው ፈተና የሀሰተኛ ሰነድ የያዙ ሰዎች ወደ ተቋሙ ሲመጡ ተደራጅተው የሚመጡ መሆኑ ነው። ወንጀለኛውን ይዞ ፖሊስ ጣቢያ እስከሚደርስ ድረስ የማምለጥ የተለያዩ አደጋዎችን የማድረስ ሁኔታዎችም ይታያሉ። ይህ ሲባል የፀጥታ ሀይሎች በቋሚነት በተቋሙ አካባቢ አለመኖራቸው ትንሽ ችግር ፈጥሯል። ከዚህ ውጪ ተቋሙ ይህ ነው የሚባል ፈተና ገጥሞት አያውቅም።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ ተቋማት ሙሉ ውክልና የተሰጠው አካል የውክልና ማስረጃውን ይዞ እያለ የኛ ተቋም በውክልናው ላይ ስላልተገለፀ ተወክላችሁ አገልግሎት አትወስዱም ሲሉ ይታያልና እዚህ ጉዳይ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሙሉቀን፡-** ይህ ትክከል ያልሆነ ጉዳይ ነው። ይህ የውክልና አረዳድ ማነስ ነው። መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ውስጥ ጉዳዬን ይፈፅምልኝ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ



**አንድ ሰው ውክልና ሲሰጥ ፎቶ ይነሳል፤ የያዘው መታወቂያም ይያያዛል፤ ሲኩሪቲ ኮድም አብሮ ይኖራል፡፡ በዚህም ሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ሁሉም ባንኮች የዚህን ተቋም የመረጃ ቋት መመልከት ይችላሉ። በውክልና ገንዘብ ማውጣት ሲፈለግ ውክልናው ከዚህ ተቋም መገኘቱን ያረጋግጣሉ። ይሄ የባንኮችን መጭበርበር ቀንሷል**

ማለት ብቻ በቂ መሆኑን ህብረተሰቡ ሊረዳ ይገባል። ተቋሙ የራሱ የቅድም ተከተል ሒደት ከሌለው በስተቀር በሀገሪቱ ያሉ ሁሉም ተቋማትን መጥቀስ እጅግ ፈታኝ በመሆኑ በጥቅሉ በመረዳት አገልግሎቱን ማግኘት ይገባቸዋል። ተቋማትም ሁሉም መጥቀስ የማይችሉ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ከተቋሙ አሰራር ጋር አገልግሎታቸውን መቃኘት ይገባቸዋል።

አንዳንዴ ግን ተገልጋዮች ይህ ችግር ገጠመን ብለው ሲመጡ ተቋሙ መልሱ አይመለከተኝም ሳይሆን የመለሳቸውን አካል ስለአሰራሩ በማስረዳት መመሪያቸውን መፈተሽ ካለባቸው በመፈተሽ ስራው የተሳለጠ እንዲሆን የማድረግ ስራ ይሰራል።

**አዲስ ዘመን፡-በተቋሙ ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ኑዛዜን የመቀበል ተግባር አለ፤ ሟች ከመሞቱ በፊት ያደረገው ኑዛዜስ እንዴት ወደ ህጋዊ ሰነድነት ሊቀየር ይችላል?**

**አቶ ሙሉቀን፡-** ኑዛዜ አንድ ሰነድ ነው። ሰዎች በሰነዶች ማረጋገጫ መጥተው ኑዛዜ መስጠት ይችላሉ። ህጉ እራሱን የቻለ አካሄድ ቢኖረውም አንድ ሰው ግን በተቋሙ መጥቶ ኑዛዜውን ልስጥ ሲል ኑዛዜ መቀበል በተቋሙ ከሚሰሩት ሰዎች መካከል በጥንቃቄ የሚከወን ነው።

ኑዛዜ በተናዛዥ ወገን የሚሰጥ ሲሆን፣ በተቋሙ የተካሄደ ኑዛዜ በህግ ዘንድ ተቀባይነት አለው። ሂደቱ ኑዛዜ አድራጊው የታደሰ መታወቂያ በማምጣት ኑዛዜውን የሚያደረግ ሲሆን፣ ተናዛዥ ሲያልፍ ያንን የኑዛዜ ወረቀት የሚመለከታቸው አካላት ሊጠቀሙበት ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል በሰፈር ሽማግሌ ፊት የተደረገ ኑዛዜ አይፀናም የሚል ውሳኔ በፍርድ ቤት ሲወሰንበት ይታያል፤ በእናንተ ተቋም የተደረገ ኑዛዜስ ይህ ችግር አይገጥመውም?**

**አቶ ሙሉቀን፡-** ኑዛዜ ይፅና አይፅና የሚለው በፍርድ ቤት የሚወሰን ጉዳይ ነው። ፍርድ ቤቱ ተናዛዥ በሚያልፍበት ጊዜ ሊያይ የሚገባቸው አካሄዶች አሉት። በዚህ ተቋም የተሰጠ ኑዛዜ ግን ከሌሎቹ የሚለየው ተናዛዥ ኑዛዜ ሲያደርግ በማጭበርበር ሊቀርብ የሚችሉ ኑዛዜዎችን ሊከላከል ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተሳለጠ አገልግሎት እየሰጠ ነው ብለዋል፤ የተቋሙ አገልግሎት ከቅሬታ የፀዳ ነው ልንል እንችላለን?**

**አቶ ሙሉቀን፡-** እሱማ ከስድስት ሺ በላይ ሰው እየተስተናገደ ከቅሬታ የፀዳን ነን ብንል የቅሬታ ማስተናገጃ ባለቋቋምን ነበር። ባለፉት አስራ አንድ ወራት ውስጥ ወደ አስራ ሰባት ሺ ሰዎች አቤቱታ አቅርበዋል። ግን ብዙ ቅሬታዎች ከተቋሙ የሚነሱት ማለትም ከአስራ ሰባት ሺው ከ95 በመቶ በላይ የሆኑ ቅሬታዎች ቅሬታውን እዛው ሰምተው በመረዳት እዛው የሚፈቱ ቅሬታዎች ናቸው። የቀረው አምስት በመቶ በአሰራር ክፍተት ሲሆን፣ እሱንም በአጭሩ ለማስተካከል ይሰራል።

ከዚህ በስተቀር ግን ያልተሟሉ መረጃዎችን ይዘው መጥተው ካልተስተናገድኩ በሚሉ አካላት የሚፈጠር ነው። አንዳንዴም ሕጋዊ መታወቂያ ኖሯቸው ግን ሳይታደስ ጥቂት ቀናት ያለፉቸውና ሌሎች ነገሮች ገጥመው ቅሬታ ሲነሳ ባለሙያው ቁጭ ብሎ ከባለ ጉዳዩ ጋር በመነጋገር ሊፈታ የሚችልበት አካሄድ አለ።

ለምሳሌ አንድ ሳምንት ሳይታደስ ያለፈ መታወቂያ ኖሮት ያላሳደሰበት ምክንያት አሳማኝ ከሆነና ወደ ተቋሙ የመጣበት ጉዳይ ፋታ የማይሰጥ ከሆነ ከሚደርሰው ጉዳት አኳያ በማሰብ አስተዳደራዊ መፍትሄ ይሰጥበታል። ይህ አስተዳደራዊ መፍትሄ ከተሰጠ በኋላ መታወቂያ አድሶ እንዲመጣ ይደረጋል ማለት ነው።

የቅሬታው መሰረት በራሱ መረጃ ያለሟሟላት ሆኖ ጉዳዩ ተስተካክሎላቸው ሲሄዱ፤ አንዳንዶች ደግሞ ከባለሙያ ጋር ተነጋግረው ያልተስተናገዱበት ምክንያት ሲነገራቸው እንዲህ አልመሰለኝም ብለው የሚሄዱም አሉ። ሌሎች ደግሞ መገልገል እየቻሉ ከአቅም ማነስ፣ ባልተገባ የባለሙያ ስነ ምግባርና ሌሎች እክሎች ሲኖሩ ግን ለመፍትሄ የተጋ አመራር መኖሩን ልናገር እወዳለሁ።

አገልግሎት ሰጪ ተቋም ሆኖ ግን ከቅሬታ የፀዳን ነን ማለት ትክክል ነው ብዬ አላምንም፤ ነገር ግን ቅሬታው በምን መልኩ እየተስተናገደ ነው የሚለውን፤ ምላሾቹና መፍትሄዎቹ ምን ይመስላሉ የሚሉትን በማየት የከፋ ችግርም የማይፈታ ቅሬታም ኖሮ አለማወቁን ልናገር እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የሙያተኞች ስነ ምግባር ላይ የሚታዩ ክፍተቶች መኖራቸውን አንዳንድ ተገልጋዮች ይናገራሉ፤ ለምሳሌ ባለጉዳይን በትህትና ተቀብሎ ተገቢውን መረጃ ከመስጠት አንፃርና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ያሉ ክፍተቶች እንዴት ይታያሉ?**

**አቶ ሙሉቀን፡-** ስነ ምግባር መከታተያ ዳይሬክተሩ የተቋሙ ዋና የስራ ሂደት ነው። በሌሎች ተቋማት እንደ ዋና የስራ ሂደት አይታይም። ዋና የስራ ሂደት ስንል በቃል ብቻ ሳይሆን በቦታው የተመደቡ ሰራተኞች ዋና የስራ ሂደት የሚያገኘውን ደመወዝ ያገኛሉ። እንዲህም ሲባል በዋና የስራ ሂደት ደረጃ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ማለት ነው።

ተጠሪነታቸውም ለዋና ዳይሬክተር ነው። እነዚህ ብዙ ጊዜ ስራቸው ያልተቋረጠ ተከታታይነት ያለው የስነ ምግባር ስልጣና በተቋሙ እንዲሰጥ ማድረግ ነው። በተለይ ህዝብን የሚያገለግል ሰው ተከታታይነት ያለው ስልጠና ይሰጠዋል። እዚህ ተቋም ላይ ማንኛውም አይነት ስልጠና ቢሰጥ ጎን ለጎን የስነ ምግባር ስልጠና ይሰጣል። የስነ ምግባር ስልጠና አንዴ ብቻ የሚሰጥ ሳይሆን በድግግሞሽ ተሰጥቶ ያ አገልጋይ ስነ ምግባርን ባህሉ እስኪያደርገው ድረስ ይሰራል።

የተቋሙ ተገልጋዮች ጠዋት ከገቡ በኋላ የሻይ እረፍት የሚባል ነገር የለም። እስከ ምሳ ሰአት አንዴም ያለማቋረጥ ለደንበኞች አገልግሎት ሲሰጡ ይውላሉ። አንዳንድ ሰው ከመድከሙ የተነሳ ቁጡ አይነት ባህሪ ሊያሳያ ቢችሉም በስልጠና እና የተለያዩ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር አገልጋዮች ሳይሰለቻቸው አገልግሎቱን የሚሰጡበት አካሄድ እንዲኖር ይሰራል።

ነገር ግን ከስር ከስር በየቅርንጫፉ የስነ ምግባር መከታተያ የቅሬታ መስሚያ ዴስክ ስላለ ስራቸው የተገልጋዩ ቅሬታ እንዳይኖር ማድረግ ነው። በዴስኩ መረጃ መስጠት ችግር ካለ እዛው እንዲፈታ የማድረግ ስራ ይሰራል። በተረፈ ደግሞ ተገልጋዩ እንዲያውቃቸው የሚገቡ ጉዳዮች በትልልቅ ቦርዶች በየቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቱ በመለጠፋቸው በማንበብ አስፈላጊውን ማስረጃ አሟልተው ተገቢውን አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ ለመናገር እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ውድ ጊዜዎን ሰውተው በቀና ትብብር ስቃለመጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑልን እጅግ በጣም እናመሰግናለን።**

**አቶ ሙሉቀን፡-** እናንተም ተቋማችንን መርጣችሁ ስለመጣችሁ አመሰግናለሁ። በዚህ አጋጣሚ በማንኛውም ሰአት ማቅረብ ለምትፈልጉት ጥያቄ በራችን ክፍት መሆኑን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ኢትዮጵያን ያበጃጁ ወርቃማ አእምሮዎች

**ከሩጫው ማዕድን የተመረቱ ወርቆች፤**

ሰሞኑን ኢትዮጵያ ፈጣሪዋን ጎላ ባለ ድምጽ እያመሰገነች፤ ልጆቿም እርሷን እያመሰገኑ መደናነቁ ደመቅ ብሏል። መከራ ያቆራመዳት አገር እጆቿን በምሥጋና ወደ ጸባኦት ዘርግታ ደስታዋን ስትገልጽ ከማየት የበለጠ ምን እርካታ ይኖራል። ለጀግኖቹ አትሌቶቻችን፣ ለአሰልጣኞቻቸው፣ ለስምሪት ሰጪዎቻቸውና በልዩ ልዩ ጉዳዮች ዙሪያ ድጋፍ ላደረጉላቸው በሙሉ ምስጋናችን ይድረሳቸውና በኀዘንና በልቅሶ በተሸበሸበው የአገሬ አንገት ላይ የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ሜዳሊያዎች ተገጥግጠው ከማየት የበለጠ ምንም የሚያስደስት ነገር የለም። እናት ዓለም! እንኳንም የሐምሌው ጭጋግ ብራ ሆኖልሽ በደስታ ፈገግ አልሽ።

እኛ ብቻ ሳንሆን 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ምክንያት ሆኖ በአሜሪካዋ ክፍለ ግዛት በኦሪገን ሰማይ ላይ የናኘውን የኢትዮጵያን አሸናፊነት ገድል፣ ጩኸትና አድናቆት በዘመናዊ የዴሲብል ሜትር መለካት ቢቻል ኖሮ ምን ያህል ከብሮና ገዝፎ አየሩን እንዳደመቀው መገመት አይከብድም። አሜሪካ ሆይ እንኳንም ብዙ ትርጉም ለሚሰጠን የደስታችን ምስክር ለመሆን አበቃሽ።

ጀግኖቹ አትሌቶቻችን ሜዳሊያውን በአንገታቸው ላይ ሲያጠልቁና አሸናፊነታቸው ሲረጋገጥ ቀድሞ በክብር ከፍ ከፍ ብሎ የሚገንነው የኢትዮጵያ ስም ሲሆን፤ የምትወከለውም በብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማዋና በብሔራዊ መዝሙሯ ነው። ባለ ወርቃማ እግር አትሌቶቿ የአገራቸውን አንገት በወርቅ፣ በብርና በነሐስ ሜዳሊያ ስላንቆጠቆጡ ልጆቻችን ሆይ ደግመን ደጋግመን ምሥጋናችን ይድረሳችሁ እንላለን። ኢትዮጵያ ሆይ! እንኳንም በልጆችሽ ደስ ተሰኘተሽ ደስ አሰኘሽን። ፈጣሪያችን ሆይ! ለአትሌቶቻችን ሙሉ ጤንነትና ብቃት ሰጥተህ የደስታችን ምንጭ ስላደረግሃቸው ክብር ምሥጋና ይድረስህ።

> **ማንም ሰው የሚከበረው ሌላውን ሲያከብር ነው። ነዎሩ የሚሰኘውም ሌላውን ፊት ሲያስቀድም ነው። አሁን አሁን እየታየ ያለው ይህን መሰሉ ልማድ ግን ለአገርም ይሁን ለታሪክ የሚበጅ ስላልሆነ በጊዜ መታረሙ አይከፋም። ምሥጋና ለሚገባው ምስጋናን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን መስጠት ያስከብራል፤ የመልካም ስብዕና መገለጫም ነው። ስለዚህም የወርቃማ አእምሮ ባለፀጎቻችንን እናክብራቸው፤ የበጎነታቸውን ውለታም ሳንሰለስት እንዘክርላቸው**

**የወርቃማ ባለ አእምሮዎች ትሩፋት፤**

የዛሬዪቱ ኢትዮጵያን መልክ በየዘመናቱ እየቀረጹና እያበጃጁ እዚህ ያደረሷትን የወርቃማ አእምሮና አገልግሎት ባለፀጎችን ትሩፋትና ዝና ማስተጋባት ያለብን ሁኔታዎች ሲቀሰቅሱንና ሲያባንኑን ብቻ መሆን ያለበት አይመስለንም። ሁሌም የአዋጅ ያህል መመስከር፣ ለልጆቻችንም መንገር፣ ልጆቻችንም ለልጆቻቸው እንዲያሳውቁ ማበረታታት ግድ የሚል ይመስለናል። እስኪ ይህንን የመመሥጋገን ሳምንት ምክንያት በማድረግ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን የወርቃማ አእምሮ ባለተሰጥኦዎች እያስታወስን እናመስግናቸው።

ስምና ዝናቸውን ቀድመን ከምንተርክላቸውና ከምናወድሳቸው የአገርና የሕዝብ ባለውለታዎች መካከል የጦር ሜዳ ጀግኖቻችን ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ። በዘመናት ውስጥ ለአገራቸው ነፃነትና ክብር ሲሉ ከጠላት ጋር እየተናነቁ በጀግንነት የወደቁት ዜጎቻችን በቁጥር የሚገለጹ አይደሉም፤ ይሞከርም ቢባል የሚቻል አይሆንም። «እነ እከሌ» ብለን እንዘርዝር ቢባልም «ዐባይን በጭልፋ» ይሉት ብጤ ይሆንብናል። በየፍልሚያው ጎራ የወደቁና ቀባሪ አጥተው የረገፉ አጽሞች ዛሬም እንደ ተከላካይ ዘብ በጽናት ቆመው ለኢትዮጵያ ክብር ሐውልት ስለሆኑ ክብርና ሞገስ ይሁንላቸው። ቀድሞውንስ ቢሆን...

**«የወታደር እናት ታጠቂ በገመድ፣**
**ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ»**

የሚለው ትንቢት እንደሚፈጸምባቸው ያውቁት የለ? ሥጋቸው ላሞራና ለዱር አራዊት ቀለብ የሆነ፤ ከቡሩ አጽማቸውም በየጉድባውና ተረተሩ እንዳልባሌ ነገር ተበታትኖ የቀረው ጀግኖቻችን የከፈሉልን ዋጋ ከግምት በላይ ስለሆነ ኒሻንና ሜዳሊያ በአንገታቸው ላይ ማጥለቅ ባይቻልም ፈጣሪ ስለ ከፈሉልን መስዋእትነትና ስለዋሉልን ውለታ ለነፍሳቸው ክብርን እንዲያጎናጽፍ በሰርክ ፀሎታችንና በቀጣዩ ታሪካችን አድምቀን ልናስታውሳቸው ይገባል። ትውልድም በየዘመኑ እንዲህ እያለ ይቀኝላቸዋል።

**በአንተ ዓላማ - በደም ትልምህ፣**
**በአንተ ትግል - በሞት ገድልህ፣**
**ይኸውና «ሰው» - ሆንኩልህ።**
**ደስ እንዳለኝ - ደስ ይበልህ፣**
**«የእኔ ጋሻ - የእኔ ወንድም፣**
**የእኔ እህት - የእኔ ክብር።**
**የሀገር ምድር - የሀገር ሰማይ፣**
**የሀገር ጀምበር - የሀገር ፀሐይ፤**
**የሀገር ዙሪያ - ክቡር አጽም፣**
**የእኔ ጋሻ - የእኔ ወንድም።**

(ከሻለቃ ክፍሌ አቦቸር፤ «የእኔ ጋሻ» የግጥም መድበል)

ዛሬም ንዳድና ቁር ሳይበግራቸው በግዳጅ ወረዳቸው ላይ ዘብ ለቆሙ ጀግኖቻችን በአገር ልብና በሕዝብ ፍቅር አክብሮታችን ይድረሳቸው። አእምሯቸው ከወርቅ የከበረ፣ ውለታቸው ከእንቁ ዋጋ የላቀ ነውና ሁሌም በክብር እንዘክራቸዋለን። ለቀጣዩ የጀግንነት ውሏቸውም እንዲህ እያልን አደራችንን እናጸናለን።

**ምሥራቅ ድንበሩ ላይ ጋሻ ሆኖ ላለው፣**
**ደቡብ ድንበሩ ላይ በጽናት ለቆመው፣**
**ሰሜን ድንበሩ ላይ ሰንደቅ ሆኖ ላለው፣**
**ምዕራብ ድንበሩ ላይ አጥር ሆኖ ላለው፣**
**በወደቁት ጀግኖች በደማቸው መሃላ፣**
**ውድ እናታችንን ኢትዮጵያን አደራ፣**
**አትዮጵያን አደራ! ኢትዮጵያን አደራ።**

ክብር በነፍሳቸው ተወራርደው ነፃነት ላጎናጸፉን። ክብር ዘብ ሆነው ለጋረዱን ጀግኖቻችን ይሁን።

**የብሩህ ባለ አእምሮዎች ወግ፤**

በርካታ ምዕራባውያን አገራት በልዩ ልዩ የሙያ ዘርፎች ለሕዝባቸው ውለታ የሚውሉ ዜጎቻቸውን የሚያሞጋግሱት «የውብ አእምሮ (Beautiful Minds) ባለ ፀጎቻችን» በሚል ማሞካሻ ነው። አድናቆታቸው በአጠራር ብቻም ሳይሆን በበርካታ የሆሊውድና የየአገሩ ፊልሞችም ሳይቀር ይከበራሉ፤ ይሞካሻሉ፤ በሽልማቶችና በስጦታዎችም ይንበሸበሻሉ።

ይህ አገላለጽ ይቆጨውና ያንገበግበው የነበረው አፍሪካዊው የጋና ደራሲ አዪ ኩዌ አርማህ እ.ኤ.አ በ1968 “The Beautyful Ones Are Not Yet Born” በሚል ርእስ አንድ ተወዳጅና ተደጋግሞ ለህትመት የበቃ መጽሐፍ ለንባብ አብቅቶ ነበር። ይህ ደራሲ በመጽሐፉ ውስጥ ደመቅ አድርጎ ለመሄስ የሞከረው የድህረ ኮሎኒያሊዝምን የጋናውያን ሕይወት ነበር።

እንደ ደራሲው እምነት ጋና ከቅኝ ገዢዎች መዳፍ ነፃ ወጥታ ድል ከተቀዳጀች በኋላ ዜጎቿ ባህላቸውንና ታሪካቸውን ንቀውና አኮስሰው እንደምን ለምዕራባውያን ቁሳቁስና ባህል ተገዢና አምላኪ እንደሆኑ ለማሳየት ሞክሯል። «እኛ ጋናውያን ገና ባለ ውብ አእምሮ ዜጎችን ማፍራት አልቻልንም፤ ለማፍራትም ዘመናት ይጠይቁናል» በማለትም አገሩንና ሕዝቡን ሞግቷል። «አካላችን ብሔራዊ ነፃነትን ቢጎናጸፍም አእምሯችን ግን ገና በእስራት ውስጥ ነው» ሲልም አገሩንና ሕዝቡን በጥበብ ሥራው አማካይነት ሄሷል።

ታሪካቸውን፣ ባህላቸውን፣ ወጋቸውን፣ ክብራቸውንና ለነፃነታቸው ምክንያት የሆኑትን የአባቶቻቸውን ገድልና ፈለግ ከመከተል ይልቅ በምዕራባውያኑ የሕይወት ዘይቤ ተማርከው አካላቸው በአገራቸው ጋና፣ መንፈሳቸውና ስሜታቸው አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ለሚንጠራወዘው የዘመኑ ትውልድንም «ገና ከተጨማለቀ የአስተሳሰብ አረንቋ ውስጥ በአሸናፊነት ስላልወጣ ትውልዱ አእምሮው አልተፈወሰም» ሲልም «የውብ አእምሮ ባለፀጋ ትውልድ ሆይ ወዴት አለህ!» በማለት በድርሰት ሥራው ውስጥ አጉልቶ ይጠይቃል።

**እኛስ?**

እኛማ! ክብር ለአገራችን ቀዳሚና ተከታይ ጀግኖቻችን ይሁንና ኢትዮጵያችንና ልጆቿ የቅኝ ገዢዎች ተንበርካኪ፣ የብሩህ አእምሮም ድሃ አልነበረችም፤ ሆናም አታውቅም፤ ልጆቿም እንደዚያው። በጀግንነቱ መስክ ብቻ ሳይሆን በሳይንስና በኪነጥበባት፣ በትምህርትና በምርምሩ መስክ ብዙ አርአያ ሰብ ዜጎችን አምጣ ወልዳለች።

አክሱም፣ ላሊበላ፣ የፋሲል ግንብ፣ የሐረር ጀጎል ጥንታዊ ከተማ፣ ውብ መስጊዶችን፣ አብያተ ክርስቲያናትንና አብያተ መንግሥታትን ያነጹት ባለ ውብ አእምሮ ልጆቿ የሥልጣኔያቸውን አሻራ ያቆዩልን ያለማንም አጋዥና የዕውቀት ብድር ነበር። የባህልና የቅርስ ባለፀጎች ያደረጉን፣ የኩራትና የክብር መደነቂያ እንድንሆን የተጉልን፣ ትናንትን ዛሬንና ነገን በሦስት የጊዜ ቀለበት አስተሳስረው ከዘመን ዘመን ዓለም በአድናቆት እየተጠቋቆመብን እንድንዘልቅ የታሪካችንን ጎዳና ያሰመሩልን እነዚሁ የክብራችን ጉልላቶች ናቸው። ሞገስና አድናቆታችን ሁሌም አብሯቸው ይዘልቃል።

የአውሮፓን ወራሪ ኃይላት መመከት ብቻም ሳይሆን ሽንፈትን እንደ ውርደት ቆጥረን ለቀጥታም ሆነ ለእጅ አዙር አገዛዝ ባዕድ ሆነን በባዕዳን ጭምር እንድንሞገስ ምክንያት ለሆኑን ሁሉ ሙገሳና አድናቆት ቢያንስባቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይደለም። እናት ዓለም ኢትዮጵያ ታሪኳም ሆነ ገድሏ እንደ ከዋክብት የበዛና የደመቀ ስለሆነ ዝርዝሩን ጀምረን ለመጨረስ የሚያዳግቱን የብዙ ትሩፋቶች ባለቤቶች ነን። ምሥጋናችን ከታላቅ አክብሮት ጋር ይድረስልን።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ልክ እንደዚህ ጸሐፊ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በመልካም ተጽእኖ ፈጣሪነት የሚጠቀሱ «የእምነት ጀግኖቻቸውን» በስምና በግብር ለመዘርዘር ሞክሮ አልሆን ሲለው «እንግዲህ ምን እላለሁ? ...ሁሉንም እንዳልዘረዝር ጊዜ ያጥረኛል። እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ከበውናል» ብሎ ሃሳቡን እንዳጠቃለለ ሁሉ፤ ይህ ብዕረኛም ይህንኑ ተግዳሮት በመጋራት ከብዙዎች መካከል ጥቂቶቹን ብቻ ቆንጥሮ በማስታወስ ሃሳቡን ሊገታ ግድ ይላል።

ደጋግመን ለመጥቀስ እንደተሞከረው መቼውንም ቢሆን «ከታሪክ መሰዊያ ላይ አመዱን ሳይሆን እሳቱን መጫር በብዙ ይመረጣል።» ታሪካችን የድል ነሺዎች ገድል የታጨቀበት ብቻ ሳይሆን፤ በብዙ ማሳያ ማረጋገጥ እንደሚቻለው ድል ተነሺነትም በስፋት እንደነበር የሚካድ አይደለም። የሚያኮሩ ብቻም ሳይሆኑ የሚያሸማቅቁ ታሪኮችም ሞልተውናል። በአጭሩ ባለ ምጡቅ አእምሮ ጀግኖች ያሉንን ያህል ትውልድን «ያመከኑ የሾተላይ ባለ አእምሮዎችም» ታሪክ የታሪካችን ሌላው ምዕራፍ መሆኑን አንክድም። ቢሆንም ግን ገፈቱን እያጠለልን በወለላ ታሪካችን ላይ ማተኮሩ የበለጠ የተሻለ ይሆናል።

አገርን ተዳፍሮ በጅምላ መውቀሱ የበጎ ሥነ ምግባር ባህርይ ባይሆንም ስህተትን መጠቆሙ ግን ለመታረም ይበጃል። ብዙ ባለ ወርቃማ አእምሮ ዜጎቻችን በአረም በሚመሰሉ አንዳንድ «ራስ ወዳድ ዜጎች» ተሸፍነውና ተጋርደው ማስተዋል ያማል፤ ያስተክዛል። ሽልማቱና ሹመቱ እንኳን ቢቀር በአደባባይ ላለማመስገን ድብብቆሽ መጫወት አገራዊ ባህላችን ለመሆን እየተንደረደረ ያለ ይመስላል። ከአሁን በፊት «አንድ ሰው ስንት ነው?» ብለን ለመጠየቅ እንደሞከርነው አንድ ሆኖ እንደ ብዙ ሰው በጓዳም ሆነ በአደባባይ እኔነትን ብቻ አንግሶ ራስን የአሸናፊዎች ሁሉ ቁንጮ ማድረግ ተዋራጅነት እንጂ የሚያስመሰግን አይደለም።

ማንም ሰው የሚከበረው ሌላውን ሲያከብር ነው። ነዎሩ የሚሰኘውም ሌላውን ፊት ሲያስቀድም ነው። አሁን አሁን እየታየ ያለው ይህን መሰሉ ልማድ ግን ለአገርም ይሁን ለታሪክ የሚበጅ ስላልሆነ በጊዜ መታረሙ አይከፋም። ምሥጋና ለሚገባው ምስጋናን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን መስጠት ያስከብራል፤ የመልካም ስብዕና መገለጫም ነው። ስለዚህም የወርቃማ አእምሮ ባለፀጎቻችንን እናክብራቸው፤ የበጎነታቸውን ውለታም ሳንሰለስት እንዘክርላቸው።

**ሰላም ይሁን!**

# ሱፐርማርኬትና የእሁድ ገበያዎች - እንደ ገበያ ማረጋጊያ አማራጮች

ሕይወት አወቀ



ሰዎች መሰረታዊ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦችን፣ የግብርና ምርቶችን፣ ወዘተ. ለመሸመት የኑሮ ደረጃቸውንና ገቢያቸውን መሠረት ያደርጋሉ፤ ከሸቀጦቹና የግብርና ምርቶቹ ዓይነት፣ መጠን፣ ጀምሮ የሚሸምቱበት ቦታም እንዲሁ ለየቅል ነው።እንደየአካባቢያቸውም ይወሰናሉ።

ለሚሸምቷቸው ምርቶች ወይም ሸቀጦች ተመጣጣኝ ዋጋ የሚጠየቅበትን፣ ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ የገበያ ቦታ አጥብቀው ያስሳሉ።የት ሰራሽነታቸውንም ይመለከታሉ።ለእዚህም ጥሩ ያሏቸውን አማራጮች ያማትራሉ።

በሀገራችን እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት ማምለጥ ያስችላል፤ ትንሽም ቢሆን ለውጥ ያመጣል ብለው ያሰቡትንና እውነትም ጥቂት ለውጥ የታየባቸውን የገበያ ቦታዎች መኀብኘትና ማዘውተራቸው የተለመደ ነው።ደንበኛ የሚለውም ነገር አንድም ከእነዚህ ሁኔታዎች ይመነጫል፡፡

ከእነዚህ ገበያዎች መካከልም የከተሜው የገበያ አማራጭ የሆነው ሱፐርማርኬት አንዱ ነው።ሱፐርማርኬት በርካታ ነገሮች በአንድ ቦታ ማግኘት የሚቻልበት ቢሆንም፣ በሀገራችን ግን ከጥቂቶች በስተቀር አብዛኛው ማህበረሰብ ከእዚህ የገበያ አማራጭ ገብቶ የመሸመት ልምድ የለውም።

ለዚህም ዋናው ምክንያት ሱፐርማርኬቶች ምርቶች በውድ ዋጋ የሚሸጡባቸው፣ መክፈል የሚችሉ ብቻ የሚስተናገዱባቸው ተደርገው ሲታዩ መኖራቸው ነው፤ በትላልቅ ሕንፃዎች ላይ መገኘታቸውን የሚፈሩም ጥቂት አይደሉም፤ የሕንፃ ኪራይ ዋጋን ጭምር ታሳቢ አድርገው የሚሸጡ ተደርገው ስለሚታሰቡም የሚይዙዋቸው ምርቶች ዋጋ የሚቀመስ እንዳልሆነ ተደርጎ ነው የሚታሰበው። ከሌሎች ጊቢያቸው ከፍተኛ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ቦታ ተደርገውም ይወሰዳሉ።

ይሁንና አሁን አሁን ይህ አመለካከት እየተቀየረ ስለመሆኑ በሱፐርማኬት ገብተው ከገበዩ ወገኖች ይደመጣል።ለወትሮው ዋጋቸው ውድ ነው የተባሉትና ከፍተኛ ገቢ ላላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ብቻ የተፈጠሩ ተደርገው የሚታዩትን የሱፐርማርኬቶች ገበያን ማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል እየተቀላቀለው ይገኛል።በተለይ ደግሞ የኑሮ ውድነት አማራጭ ገበያዎችን ግድ ባለበት በዚህ ወቅት ሱፐርማርኬቶች እየተፈለጉ ናቸው።

አዲስ አበባ እንደ አባድር፣ ሸዋና ባምቢስ የመሳሰሉት ሱፐርማርኬቶች ያሏት ብትሆንም አብዛኛውን ሕዝብ በመድረስ በኩል ግን ክፍተት ነበረባቸው።በዚህ የተነሳም ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ገበያዎቹ የጥቂቶች ተደርገው ይታዩም ነበር።ሱፐር ማርኬቶች ላይ አሁን ለውጦች እየታዩ ናቸው።በተመጣጣኝ ዋጋው ጭምር በማህበረሰቡ ዘንድ እየተለመደ የመጣው የሱፐርማርኬት ገበያ፣ በተለያዩ አካባቢዎች እየስፋፋም ይገኛል።

ባለቤትነቱ የሼክ መሀመድ አላሙዲን የሆነው ሆራይዞን ፕላንቴሽን ክዊንስ ሱፐር ማርኬትን በአዲስ አበባ ከፍቷል፤ ሱፐርማርኬቱ በተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች ቅርንጫፎችን ከፍቶ እየሠራ ሲሆን፣ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለገበያ ያቀርባል።የግብርና ምርቶቹን ከእህት ኩባንያዎቹ ያገኛል።ይህ መሆኑም በንግድ ሰንሰለት መራዘም የሚደርስ የዋጋ ጭማሪን ማስቀረት ይቻላል።ሌሎች በርካታ ሱፐር ማርኬቶችም ገበያውን ተቀላቅለዋል።

አራት ኪሎ አካባቢ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በቅርብ ርቀት በሚገኝ ሕንፃ አንደኛ ፎቅ ላይ ያለው አራዳ ማርትም ሌላው ሱፐርማርኬት ነው።በዚህ ሱፐርማርኬት ሲገበዩ ያገኘናቸው ሸማቾች በመኖሪያ አካባቢያቸው ከሚገኙ የጉልትም ይሁን ሌሎች የገበያ ቦታዎች በተሻለ ሱፐርማርኬቶች ተመራጭ እየሆኑ መምጣታቸውን ይገልጻሉ።መሰል የገበያ አማራጮችን ማህበረሰቡ ቢለምዳቸው መልካም ነው ሲሉም ይመክራሉ።

ከሱፐር ማርኬቱ አትክልትና ፍራፍሬ እየሸመተች ያገኘናት ወይዘሪት ጸሐይ ሞላ፤ በምትሠራበት አካባቢ እንዲህ ዓይነት የገበያ አማራጭ ማግኘት በመቻሏ ደስተኛ ናት፤ ሱፐርማርኬቱ ለመኖሪያ ቤቷ የራቀ መሆኑን ጠቅሳ፣ ለሥራ በወጣችበት ወይም በሥራ መውጫ ሰዓት ወደ ሱፐርማርኬቱ ሄዳ የሚያስፈልጓትን በሙሉ ሸማምታ ወደ ቤቷ እንደምትሄድ ትናገራለች።በመኖሪያ አካባቢዋ ካለው ገበያ ጋር በማነጻጸርም አራዳ ማርት ላይ እያገኘች ያለችው አገልግሎት የተሻለ እንደሆነ ነው የምትጠቅሰው።

ለአብነትም በጉልት ገበያ ላይ ሰዎች የፈለጉትን መርጠው ማንሳት እንደማይችሉና ሱፐርማርኬት ላይ ሲሆን ግን ሸማቹ ጥራት ያለውን ማንኛውንም ምርት በእጁ እያነሳ መርጦ መውሰድ መቻሉንም እንደ አንድ መልካም አማራጭ አድርጋ ትወስደዋለች።በዋጋም ቢሆን በትንሹ ከአንድ ብር ጀምሮ ቅናሽ ያለው መሆኑን ጠቅሳ፣ ሱፐርማርኬት ተመራጭ መሆኑን እየተገነዘበች መምጣቷን ተናግራለች። ከሰፈር ሰፈር ደግሞ ገበያው የሚለያይ እንደሆነ ነው የጠቀሰችው፡፡

እርሷ በምትኖርበት ጀሞ አካባቢ ጉልት ላይ የምርቶች ዋጋ ውድ እንደሆነ ጠቅሳ፣ መርካቶ አካባቢ ቢኬድ ቅናሽ እንደሆነ በንጽጽር ገልጻለች።ይሁንና መሰል ሱፐርማርኬቶች በየአካባቢው ቢኖሩ ማህበረሰቡን በተለያየ መንገድ ማለትም በዋጋም ይሁን በምርት ጥራት የተሻለ ተጠቃሚ እንደሚያደርጉ ነው ያብራራችው።ደህንነቱ በተጠበቀና ምቹ በሆነ ቦታ መገበያየት በራሱ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ እንደሚያደርገውም ያስረዳችው፡፡

ከዚሁ ሱፐርማርኬት ሳንወጣ ፍራፍሬ እየሸመቱ ያገኘናቸው ወጣት መሠረት በልሁ እና አሸናፊ ገብሬም እንዲሁ ጉልትን ጨምሮ በአካባቢያቸው ከሚገኘው ገበያ ወይም መደብር ይልቅ ሱፐርማርኬት የተሻለ ስለመሆኑ እየተረዱ መምጣቸውን ይናገራሉ።ምንም እንኳን ደረጃቸውን የጠበቁ ሱፐርማርኬቶች በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ አለመሆናቸውን ጠቅሰው፣ ለአካባቢው ሰው ከአንድ ብር ልዩነት ጀምሮ በጥራት በማቅረብ ሰዎች እንደፈለጉ መርጠው መግዛት መቻላቸው መልካም እንደሆነ ነው የገለጹት።

‹‹በብዙ ሰዎች አስተሳሰብ የሱፐርማርኬቶች ዋጋ ውድ ተደርጎ ይታያል።ሸማቾች ግን ሱፐርማርኬቶችን በሩቅ ሆነው ዋጋቸው አይቻልም ብለው እንደሚሸሹዋቸው ይናገራሉ።ይሁንና ዋጋው እንደሚታሰበው ብዙ ልዩነት የለውም።እንዲያውም የተሻለና ጥራት ያለው ምርት የሚገኘው በሱፐርማርኬቶች ውስጥ ነው›› በማለት የሱፐርማርኬቶችን ተመራጭነት ወጣት መሠረትና አሸናፊ ያስረዳሉ።

ከዚህ በተጨማሪም በሱፐርማርኬቶች ውስጥ ዋጋ ስንት ነው? ብሎ መጠየቅና መከራከር አለመኖሩ በራሱ ጊዜን መቆጠብ የሚያስችልና ተመራጭ የሚያደርጋቸው ነው ሲሉ ያብራራሉ።የሁሉም ምርቶች ዋጋ በግልጽ በጽሑፍ የቀረበ ሲሆን፣ ሸማቹ የፈለገውን እና የመረጠውን በሚፈልገው መጠን ገዝቶ ይወጣል።ይህ ደግሞ ሊበረታታና በማህበረሰቡ ዘንድም ሊለመድ የሚገባው የገበያ አማራጭ ነው ይላሉ።

አራዳ ማርት ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ለየት ያለ አሠራር ይዞ ስለመቅረቡ የአራዳ ማርት ባለቤት አቶ ታምራት ዘውዴ ይገልጻሉ፤ ድርጅቱ ከሌሎች የገበያ ቦታዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ኅብረተሰቡ ዘንድ ለመድረስ ሲነሳ ማህበረሰቡን ቤተሰብ በማድረግ መሆኑን ይናገራሉ።የምርቶቹ ዋጋ መንግሥት አማራጭ ብሎ ካቀረባቸው የእሁድ ገበያዎች ሳይቀር የአንድ ብር ቅናሽ እንደሚኖረው፣ አልያም እኩል ዋጋ የሚኖርበት ጊዜ እንዳለ ነው የሚያብራሩት።

አራዳ ማርት ከተጀመረ ዘጠኝ ወራትን ብቻ ያስቆጠረ እንደሆነና በዚህ ጊዜ ውስጥም ከጠበቁት በላይ አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነና በአሁኑ ወቅትም በአማካኝ በቀን ከ250 እስከ 300 ሰው እያስተናገደ መሆኑን ያብራራሉ።ሱፐርማርኬቱ የሸቀጦች ዋጋ እየናረ ባለበት በዚህ ወቅት ጥራት ያለውን ተፈላጊ ምርት መጠነኛ በሆነ ቅናሽ ይዞ መቅረቡ ተመራጭ እንዳደረገው አቶ ታምራት ይገልጻሉ፡፡

ለዋጋ ውድነት ዋናው በመሀል የሚኖረው ደላላና ረጅሙ ሰንሰለት ስለመሆኑ አቶ ታምራት ይናገራሉ።ሱፐርማርኬቱ የግብርና ምርቶችን በቀጥታ ከአምራቹ እንደሚያመጣና መጠነኛ ትርፍ አግኝቶ ለሸማቾች እንደሚያቀርብ ነው ያብራሩት።ረጅሙን ሰንሰለት በማሳጠር እንዲሁም አግባብ ያልሆነ ጭማሪ አለማድረግ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ያስችላል ይላሉ።

በቀጣይም ተደራሽነትን ለማስፋት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ቤት ለቤት የማድረስ ሥራ እንደሚጀምሩ የተናገሩት አቶ ታምራት፤ በተለይም አዲስ አበባ ከተማ ላይ መሰል የቢዝነስ ሞዴል ተግባራዊ ማድረግ ለማህበረሰቡም ሆነ ለመንግሥት ጠቃሚ እንደሆነ ነው አስታውቀዋል።ሰዎችን ለመድረስ የግድ ወጪ አውጥቶ በየአካባቢው ሕንፃ መከራየት የግድ እንዳልሆነና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ቅርንጫፎችን ማስፋትን አቅደዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የኑሮ ውድነትን ለመቆጣጠር ሌሎች አማራጮች ተደርገው በመንግሥትም በሕዝቡም የተያዙት የህብረት ሥራ ማህበራት ናቸው።ማህበራቱ በሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት በኩል በተመጣጣኝ ዋጋ የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶችን ለሸማቾች እያቀረቡ ይገኛሉ።በአዲስ አበባ የህብረት ሥራ ማህበራቱ ሚና እየሰፋ ሲሆን፣ የከተማ አስተዳደሩ ለማህበራቱ ገንዘብ በተዘዋዋሪ ፈንድ በመስጠትም በማህበራቱ ይበልጥ እንዲሠራ እያደረገ ያለው።

‹‹እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት ለማረጋጋት መንግሥት ይጠቅማሉ ባላቸው የህብረት ሥራ ማህበራት በኩል እየሠራ ይገኛል፡፡›› የሚሉት በኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ወይዘሮ አያልሰው ወርቅነህ፤ በተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦችና በግብርና ምርት አቅርቦት ዙሪያ ያለውን ችግር ለመፍታት የህብረት ሥራ ማህበራት አማራጮች መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የህብረት ሥራ ማህበራትን እየተጠቀመ መሆኑንም ነው የሚገልጹት።ማህበራቱ ካላቸው ጉልህ ሚና አንጻር የገበያ ተደራሽነታቸውን ለማስፋትም በርካታ ሥራዎችን በማከናወን የድርሻውን እየተወጣ ይገኛል።

በመሆኑም በምርት አቅርቦትና ግብይት ላይ ከፍተኛ ድርሻ ካላቸው አምራቾችና ሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራት፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ ኢንዱስትሪዎች፣ አስመጪዎች፣ አቀናባሪዎችና ታላላቅ ግዢ ከሚፈጽሙ ተቋማት ጋር ቀጥተኛ የግብይት ትስስር መድረኮች በማመቻቸትና ግብይት እንዲፈጸም የውል ስምምነቶችን በማድረግ የግብርናና የሸቀጥ ምርት አቅርቦት ችግር እንዲፈታ ጥረት በማድረግ ላይ ነው፡፡

አሁን እየታየ ያለው የኑሮ ውድነት በአገር ውስጥ ካለው ችግር በተጨማሪ በውጭ ዓለም ያለው ውጥረትም እንደምክንያት የሚጠቀስና ችግሩን ይበልጥ እንዳባባሰው የጠቀሱት ዳይሬክተሯ፤ ዜጎች በእጅጉ እየተፈተኑበት ያለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡

ከእነዚህም መካከል ጤናማ የግብይት ሥርዓትን በማስፈን አምራችና ሸማቹን በቀጥታ ለማገናኘት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አማካኝነት የተጀመረው የእሁድ ገበያ የዋጋ ንረትን ለማርገብ ብሎም ገበያን ለማረጋጋት ጉልህ ድርሻ እየተጫወተ ይገኛል።

ወራት ያስቆጠረው የእሁድ ገበያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ ከአስር በማይበልጡ ቦታዎች ነው የተጀመረው።በአሁኑ ወቅት የክልል ከተሞችን ሳይጨምር በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ 50 በሚደርሱ አካባቢዎች ግብይት በቋሚነት እየተካሄደ የሚገኝ ሲሆን፣ ኅብረተሰቡ ዘንድ ይበልጥ ለመድረስ በቅርቡ ቅዳሜን ጨምሮ ገበያው እንዲኖር እንደሚደረግ ተጠቁሟል።

ለዚህም ትልቅ ድርሻ ያላቸው የህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከርና ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ዋነው ጉዳይ ነው።በተለይም በከተሞች የሚስተዋለውን የምርት እጥረትና የሸቀጦች ዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ማህበራቱ ከመቼውም ጊዜ በተለየ የጎላ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ።ይህም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የመቃወም አባዜ.......

**በፍቃዱ ከተማ**

የዛሬው ትዝብቴ መነሻ የኤፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ባለፈው ሳምንት የኢትዮጵያን የአትሌቲክስ ድል አስመልክተው ያስተላለፉትን የእናመስግን ጥሪ የሚቃወሙ ሰዎች ናቸው።

ይህንን ተግባር ለማውገዝ የተነሳሁት ጉዳዩ ብዙ ኢትዮጵያውንን ባይመለከትም የጥቂቶች እኩይ ተግባርና አስተሳሰብ ብዙኃንን የመመረዝ አቅም አለው ብዬ ስለማምን ነው። ለሀገራችን ኢትዮጵያ ዕድገትና ብልጽግና ሚሊዮኖች ጉልበትና ዕውቀታቸውን መስዋዕት አድርገው የሚለፉትን ያህል ከእያንዳንዱ ጉዳይ ሰበዝ እየመዘዙ የትችትና የንትርክ መድረክ ለመፍጠር የሚታትሩም ጥቂቶች አይደሉም።

እነዚህን ዓይነት ግለሰቦች ምንም ዓይነት መልካም ሥራ ይሥራ ለጉዳዩ የሕግና የሞራል ሽፋን ፈልገው ለመተቸት መሮጥ የእንጀራቸው ምንጭ አድርገው የሚወስዱት ጉዳይ ነው። ስለሆነም የበጋ መስኖም ይሥራ የአቅመ ደካሞች ቤት ይታደስ አንካሳና ሰንካላ ሰበቦችን እየመዘዙ ለመተቸት ከመሮጥ አይቆጠቡም። እነኚህን መሰል ግለሰቦች በሕይወታችሁ ምን በጎ ሥራ ሠራችሁ ተብለው ቢጠየቁ የሚሰጡት ምንም ምላሽ ባይኖርም እንዲሁ መተቸትና መንቀፋቸውን ግን አይተውም።

እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በቤተሰብ፣ በተቋምና በሀገር ደረጃ በጎ ተግባር እንዳይቀጥል እንቅፋት ከመሆናቸውም በላይ ለዕድገትና ለሰላም በጎ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ለማሸማቀቅና ከበጎ ተግባራቸው ለማደናቀፍ እንቅልፍ አጥተው የሚኖሩ ናቸው። መልካም ሰው በመጥፎ ነገሮች መካከል በጎና ቀናውን አይቶ እሷኑ ለማሳደግ ሲጥር የዚህ ተቃራኒ የሆኑ እነዚህ እኩያን ግን ከበጎ ተግባር ውስጥ ስንጥር የምታክል ግድፈት ፈልገውና የዝሆን ያህል አተልቀው ብርሃንን ለማጨለም ሲሮጡ ውለው ሲሮጡ ያድራሉ።

በዚህ ጽሑፌ ትኩረት እንዲሰጠው የምፈልገው ጉዳይ ትችት ወይም ተቃውሞ ፈጽሞ አስፈላጊ አይደለም እያልኩ አለመሆኔን ነው። ለማቅናትና ለማሳደግ መተቸትና እየሠሩ መቃወምማ ማለፊያና የሚደገፍ ቅዱስ ተግባር ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። የሚያስጠላወና የማይደገፈው ግን ለመቃወም ሲሉ በጎውንና ደጉን ሁሉ በጭፍን መተቸትና መቃወሙ ነው።

በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ ጠላቶቿ ያለ የሌለ አቅማቸውን አስተባብረው የዘመቱበት እንዲህ ዓይነት ጊዜ በታሪካችን ያለ አይመስለኝም። ለሁላችንም ግልጽ እንደሆነው የኢትዮጵያ ጠላቶች ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ በተቀናጀና በተናበበ ሁኔታ ሀገር የማፍረስ ተልዕኮን አንግበው እየተንቀሳቀሱ ነው። ምስጋናና ክብር ለሀገራችን የተቀናጀ የጸጥታ ኃይልና የደህንነት ተቋማት ይሁን እንጂ ጠላቶቻችን ያሰቡትን የጥፋትና ሀገር የማፍረስ ተልዕኮ ግማሹን እንኳ ቢያሳኩት ኖሮ እውን እንደ ሀገር እንቀጥል ነበርን የሚለው ጉዳይ በጥያቄ ምልክት ውስጥ ይቀመጥ ነበር።

በተለይም በለውጡ ዘመን ኮሮና፣ ድርቅና ጎርፍን ከመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች ጀምሮ በሀገራችን ላይ የታቀዱ ከባባድ የሽብር ዕቅዶች ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ውድ ዋጋ አስከፍለዋል። በዚህ ሂደት ውስጥ የነበረው አማራጭ ለችግር እጅ ሰጥቶ ተስፋ ቆርጦ መቀመጥ ወይም ችግሮች እንደመልካም አጋጣሚ ወስዶ በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሃገራዊ ብልጽግናን እውን ማድረግ ነበር። ከእነዚህ ሁለት አማራጮች መካከል ኢትዮጵያ የመረጠችው ፈተና ቢኖርም ተቋቁሞ ድል ማድረግ ይቻላል የሚለውን ነበር።

በበጋ ስንዴ ምርት የተገኘው አመርቂ ውጤት፣ በኤክስፖርት ገቢ የታየ ከፍተኛ መሻሻል፣ በፕሮጀክቶች አፈጻጸም የታየው እመርታ ኢትዮጵያ በፈተና ውስጥ ሆና ካስመዘገበቻቸው ወርቃማ ውጤቶች የሚደመሩ ናቸው። ኢትዮጵያን የሚመጥኑ ተቋማትን ለመገንባት የተደረገው ርብርብና የተገኘው አኩሪ ውጤትም መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ በሆነበት ሁኔታ የተገኘ ሳይሆን በአንድ እጅ ፈተናን እየተጋፈጡ በሌላው እጅ ልማትን እያሳለጡ ኢትዮጵያውያን ያስመዘገቡት አኩሪ ውጤት ነው።

ከእነዚህ ድሎቻችን በተጨማሪ በሀገራችን የሰፈነውን የፖለቲካ ውጥረት ረገብ ያደረገውና በኢትዮጵያውያን ኅብረ ብሔራዊ አንድነት አሜሪካ ኦሪጎን ላይ የተመዘገበው የዓለም የአትሌቲክስ ሻምፒዮና ድል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ምንም እንኳን በፈተና ውስጥ ቢያልፉም በመጨረሻ ድል ከማስመዝገብ የሚያግዳቸው ምድራዊ ኃይል እንደሌለ ያሳየ ልዩ ክስተት ነበር። በዚህ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አንደኛ ከዓለም ደግሞ ልዕለ ኃያሏን ሃገር አሜሪካን በመከተል ሁለተኛ ሆና አጠናቃለች። ኢትዮጵያ ብዙ ፈተና ውስጥ ሆና የተመዘገበው ይህ ዓለም አቀፍ ድል ለኢትዮጵያውያን ከሻምፒዮንነት የዘለለ ልዩ ትርጉም ነበረው። ለዚህም ይመስላል ጀግናዋ አትሌትና የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ ድሉ ከሜዳሊያም በላይ ስትል የገለጸችው።

ሀገራችን እያለፈችበት ያለውን የፈተና መንገድና በዚህ ውስጥ የተመዘገቡትን ድሎችም አስመልክቶም ነበር የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለመላ ኢትዮጵያውያን “በጽኑ ማንነታችንና በፈጣሪ እገዛ ለምንታመነው እኛ ሁሌም ከክረምቱ ባሻገር የሚመጣው ብሩህ ጸደይ ጎልቶ ይታየናል፤ ከጨለማው ማዶ ደማቅ ብርሃን እንዳለ እናውቃለን። የትናንቱን ጨለማ እንዳለፍነው ሁሉ የዛሬውን ጽልመት የማንሻገርበት ምክንያት እንደሌለ እያመንን፣ ብርታትና ጥንካሬውን ለሚቸረን ፈጣሪ ዛሬም ምስጋና ከማቅረብ አንቦዝንም” የሚል መልዕክት ያስተላለፉት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም “አመስጋኝነት ያለፈውን ዘመን በአሸናፊነት፣ ያለንበትን ወቅት በዕድለኝነት፣ መጪውን ጊዜ ደግሞ በብሩህ ተስፋ እንድንመለከተው የሚያደርግ ታላቅ ኃይል አለው። በአንጻሩ አማራሪነትና ምስጋና ቢስነት የተሸናፊነትና የዕድለ ቢስነት ሥነ ልቡናን ይፈጥራል። ራሳችንንና ሌሎችን በአዎንታዊነትና በፍቅር መመልከት እንዳንችልም ያደርገናል።

በምሬትና በምስጋና ቢስነት የተጠመደ ግለሰብም ሆነ ሕዝብ የጎደለው እንጂ በእጁ ያለው ጸጋ አይታየውም። የደረሰበት በደል እንጂ የተሰጠው ዕድል አይጎላለትም። የሚመጣው መከራ እንጂ ከፊቱ ያለው ደስታ በጎሊናው አይሳልም። አመስጋኝ ሰው በመከራውና በጭንቁ ውስጥ ድሉንና ዕድሉን ማየት የሚችል ነው። ከወጀቡና ከማዕበሉ ይልቅ የመርከቧን ጥንካሬ ያያል። ከፈተናና ከችግሩ ግዝፈት ይልቅ፣ ሁሉንም በአንድነትና በፈጣሪ ርዳታ ለማሸነፍ የሚቻል መሆኑን ያስባል።

የአክሱምና ቀደምት ሥልጣኔዎች፣ የላሊበላና በዙሪያው የነበሩ ምሥጢራዊ የኪነ ሕንጻ እምርታዎች፣ በሐረርና በዙሪያው አብቦ የነበረው የከተሜነት መነቃቃትና ዕድገት፣ በጊቤ ዙሪያ የነበሩ ንግድን ከግብርና ያጣመሩ ሥልጣኔዎች፤ በገዳ ሥርዓት ዴሞክራሲን የማስተዋወቅ ጥረቶች፤ በወላይታ፣ በከምባታ፣ በሐላባ፣ በሐድያ፣ በዳውሮና ከፋ ዙሪያ የነበሩ ከመካከለኛው ምሥራቅ እስከ አውሮፓ ድረስ የንግድና የዲፕሎማሲ ግንኙነት የተመሠረተባቸው አስተዳደሮች፤ በጎንደር የተማከለ መንግሥታዊ አስተዳደር የመፍጠር ሙከራ፤ በአፋርና በሶማሌ የነበረው መረጃንና ማዕከላዊነትን መሠረት ያደረገው የአስተዳደር ሥርዓት፣ በጋምቤላ የነበረው ለሴቶች የተለየ የክብር ቦታ የሚሰጠው ሥልጣኔ፣ በቤኒሻንጉል የነበረው የሙዚቃና የሙዚቃ መሣሪያዎች ልህቀት፤ እንዲህም በሌሎቹም አካባቢዎች ታይተው የነበሩትን ሥልጣኔዎች ወደ ኋላ ዞር ብለን በማየት ልንኮራባቸው የሚገቡ ሀብቶቻችን ናቸው። የምንኮራባቸውን ትናንቶች የሰጠንን የኢትዮጵያን አምላክ ማመስገን ያለብንም ለዚህ ነው። ” ሲሉ ኢትዮጵያውያን ጊዜያዊውንና የሚያልፈውን ፈተና ሳይሆን ፈጣሪ ያደላቸውን በረከትና መጻዒ ድል ተመልክተው እንደየእምነታቸው አምላካቸውን እንዲያመሰግኑ ጥሪ ያስተላለፉት።

ይህንኑ መልዕክት በመቀበል በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙ የሃይማኖት ተቋማትና መሥሪያ ቤቶች ምዕመኖቻቸውንና ሠራተኞቻቸውን በማስተባበር የምስጋና መርሐ ግብር አካሂደዋል። ከዚሁ በተቃራኒም ጥቂቶችና ትችት የሁል ጊዜ ተግባራቸው የሆኑ ግለሰቦች ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ጥሪ በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ የተደረገ ጣልቃ ገብነት በማስመሰልና ፍጹም የማይገናኙ ምክንያቶችን በመዘርዘር ለመተቸት ሲዳዱ ተስተውሏል። ይሁንና ሕዝቦች እንደየእምነታቸው ፈጣያሪቻቸውን እንዲያመሰግኑ ትዕዛዝ ሳይሆን ጥሪ ማቅረብ መላ ሕዝቦቿ ሃይማኖተኛ ለሆኑባት ሃገር ክብር የሚመጥን ቅዱስ ተግባር መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። ፈጣሪ ሲመሰገን የሚጠላው ሳጥናኤል ብቻ መሆኑም ሊሰመርበት ይገባል!

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ የአልቃይዳን መሪ ካቡል ውስጥ መግደሏን ገለጸች

አሜሪካ የአልቃይዳውን መሪ አይማን አል-ዛዋሂሪን በአፍጋኒስታን ዋና ከተማ ካቡል ባካሄደችው የድሮን ጥቃት መግደሏን ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አስታወቁ። የአሜሪካ የደህንነት መስሪያ ቤት ሲአይኤ ባሳለፍነው ዕሁድ ካቡል ውስጥ ባካሄደው የፀረ-ሽብር ዘመቻ ዛዋሂሪን መግደል ችሏል።

ፕሬዚዳንት ባይደን ዛዋሂሪ «በአሜሪካ ዜጎች ላይ ግድያ እና ጥቃትን የቀረጸ ሰው ነው»ብለዋል። አክለውም «አሁን ፍትህ ተሰጥቷል፤ ይህ የአሸባሪ ቡድን መሪ ከዚህ በኋላ በሕይወት የለም» ሲሉም ግድያውን ተከትሎ በሰጡት መግለጫ ላይ ተናግረዋል።

ዛዋሂሪ ከቀድሞው የአል-ቃይዳ መሪ ቢን ላደን ጋር በመሆን የ9/11 ጥቃትን የመራ ሲሆን አሜሪካ ለረጅም አመታት ስታፈላልገው የቆየች የሽብር ቡድኑ መሪ ነው። የኦሳማ ቢን-ላደን ሕልፈትን ተከትሎም አል-ቃይዳን ሲመራ ቆይቷል። የአሜሪካ ባለስልጣናት እንዳሉት ዛዋሂሪ በአንድ በጥብቅ በሚጠበቅ ቤት በረንዳ ላይ ተቀምጦ ባለበት ነው የአሜሪካ ሰው አልባ አውሮፕላን ሁለት ሚሳኤሎችን ተኩሶ የገደለው።



እንዲሁም በቤቱ ውስጥ የነበሩ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው እና ዛዋሂሪ ብቻ ተነጥሎ መገደሉንም አክለው ተናግረዋል። ባይደን በ71 አመቱ የአልቃይዳ መሪ ላይ እርምጃውን ለመውሰድ ለወራት እቅድ ከወጣ በኋላ «የተመጠነ እና ትክክለኛውን ኢላማ የመታ ጥቃት» እንዲሰነዘር የመጨረ ሻውን የይለፍ ፍቃድ መስጠታቸውን ተናግ ረዋል።

የሽብር ቡድን መሪው ግድያም እ.ኤ.አ. በ2001 በተፈጸመው ጥቃት 3,000 የሚጠጉ ወዳጅ፣ ቤተሰ ቦቻቸውን ላጡ አሜሪካውያን ለኀዘናቸው መልስ የሚሆን የመጨረሻውን መደምደሚያ የሚሰጥ እርምጃ ነው። «የቱንም ያህል ጊዜ ቢፈጅም፣ የትም ብትደብቁ፣ ለሕዝባችን ስጋት የሆነ አካል ካለ አሜሪካ ታገኝሃለች ቀጥሎም ትዘርርሃለች» ያሉት ባይደን አክለውም «አገራችንን እና ሕዝባችንን ከመከላከል ወደ ኋላ አንልም» ሲሉም ገልጸዋል።

ባይደን ዛዋሂሪ እ.ኤ.አ በጥቅምት 2000 በኤደን የአሜሪካ የባህርኃይል አውዳሚ ላይ በተሰነዘረ የአጥፍቶ መጥፋት ጥቃት 17 የአሜሪካ መርከበኞችን የገደለውን ጥቃት መርቷል ሲሉ ተናግረዋል። እንዲሁም ለ223 ሰዎች ህልፈት ምክንያት የሆኑት በ1998 በኬንያ እና ታንዛኒያ በአሜሪካ ኤምባሲዎች ላይ የተፈፀሙትን ጥቃቶች በማስተባበር ዛዋሂሪ ኃላፊነት እንዳለበትም አውስተዋል።

ፕሬዚዳንት ባይደን አፍጋኒስታን ከእንግዲህ የአሸባሪዎች መሸሸጊያ አትሆንም ሲሉም አጥብቀው ተናግረዋል። የታሊባን ቃል አቀባይ የአሜሪካን ዘመቻ ዓለም አቀፍ መርሆችን የጣሰ ነው ሲሉ ገልፀውታል። «እንዲህ ያሉ ድርጊቶች ላለፉት 20 ዓመታት ያልተሳኩ ሙከራዎችን መደጋገም ናቸው። ድርጊቱም የአሜሪካን፣ የአፍጋኒስታንን ብሎም የቀጠናውን ጥቅም የሚፃረር ነው» ብለዋል። የአሜሪካ ባለስልጣናት በበኩላቸው ኦፕሬሽኑ ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን ቢቢሲ በዘገባው አመልክቷል።

## በሕንድ አንድ ሰው በዝንጀሮ ፈንጣጣ ሲሞት 20 ሰዎች እንዲለዩ ተደርገዋል


በሕንድ ኬሬላ በተባለች ግዛት ውስጥ አንድ ሰው በዝንጀሮ ፈንጣጣ መሞቱ ተዘገበ። የ22 ዓመቱ ግለሰብ ከዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ ነበር ወደ ሕንዷ ኬሬላ ግዛት በቅርቡ የተጓዘው። የግዛቲቱ የጤና ሚኒስትር ቬና ጆርጅ እንዳሉት፣ ግለሰቡ ውጭ አገር ሳለ በዝንጀሮ ፈንጣጣ መያዙ ታውቋል። በዚህም ከአፍሪካ ውጪ በዝንጀሮ ፈንጣጣ የሞተ አራተኛው ሰው ነው።

ከግለሰቡ ጋር የቅርብ ንክኪ የነበራቸው 20 ሰዎችም ተለይተው እንዲቆዩ ተደርገዋል። እነዚህም ቤተሰቦቹ፣ ጓደኞቹና በቅርቡ አብረውት እግር ኳስ የተጫወቱ 9 ሰዎች ናቸው። የዝንጀሮ ፈንጣጣ የሚከሰተው ፈንጣጣ ከሚያስይዘው ቫይረስ ጋር ተቀራራቢ በሆነ የቫይረስ ዝርያ ነው። የዓለም ጤና ድርጅት የዝንጀሮ ፈንጣጣ አጣዳፊ ዓለም አቀፍ የጤና ቀውስ እንደሆነ ከጥቂት ሳምንት በፊት ማወጁ ይታወሳል።

የግለሰቡን ሕልፈት ተከትሎ በሕንድ የአስቸኳይ ጊዜ ኮሚቴ ተቋቁሞ የሟቹን የሕክምና ታሪክ እየመረመረ እንደሆነ ተገልጿል። ግለሰቡ ትኩሳት የነበረው ሲሆን፣ ሆስፒታል ሲወሰድ ሰውነቱ እብጠት ነበረው። ነገር ግን ሽፍታ ስላልታየበት የዝንጀሮ ፈንጣጣ ሊሆን እንደሚችል አልተገመተም። በዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ ሳለ በቫይረሱ መያዙ ቢነገረውም፣ ቤተሰቡ ለጤና ሚኒስትር ያሳወቀው ዘግይቶ ነው።

ሆስፒታል ሳለ ሕመም እንደጸናበትና የመተንፈሻ መርጃ (ቬንትሌተር) ታግዞ ይተነፍስ እንደነበርም ተገልጿል። ከዚያም ሕመሙ የዝንጀሮ ፈንጣጣ እንደሆነ ታውቋል። ግለሰቡ ሕክምና ሳያገኝ ለምን እንደዘገየ እየተጣራ እንደሚገኝ የጤና ሚኒስትሯ ተናግረዋል።

ከዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ ወደ ኬሬላ ግዛት አብረውት የተጓዙ ሰዎችም ስለ ጉዳዩ እንዲያውቁ ተደርጓል። ከግለሰቡ ጋር የቅርብ ንክኪ ስላልነበራቸው ግን እምብዛም አያሰጋም ተብሏል። ሕንድ ውስጥ




እስካሁን አራት ሰዎች በዝንጀሮ ፈንጣጣ መያዛቸው ታውቋል። ሦስቱ በኬሬላ ግዛት ሲኖሩ አንዱ በዴልሂ ይገኛል። መጀመሪያ የተገኘው ታማሚ በኬሬላ ሆስፒታል ታክሞ ማገገሙን ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# ፕሮፌሰር ክላውድ ሰምነር (1919-2012)

ገርማ መንግሥቴ

ብዙ ጊዜ እንደምንለው ባለውለታዎቻችን ብዙ ናቸው። የዛሬውን አያድርገውና፣ ጠላት የለንም እስከንል ድረስ ወዳጆቻችን ተቆጥረው አያልቁም ነበር። ከአፍሪካ እስከ ምስራቁ አለም - ሩሲያ፣ ቻይና ... ድረስ፤ ምእራቡን አካልሎ፣ አሜሪካንን ጨምሮ፤ እሲያን አዳምሮ ወዘተርፈ ሁሉ ጥብቅ ወዳጆቻችን፤ አጋርና አርአያነታችንን ፈላጊዎች ነበሩ። ወደ ግለሰቦችም ስንመጣ ጉዳዩ ያውና ሲበዛም ተመሳሳይ ነው። ለዚህ ደግሞ ከጥንታዊያኑ ባለቅኔ ሆሜር ጀምሮ እንደ እነ ፕሮፌሰር ፓኦሎ ማራሲኒ፣ አሌሳንድሮ ባውዚ፣ ሪቻርድ ፓንክረስት እና ሀሮልድ ማርከስ ያሉትን መጥቀሱ ብቻ በቂ ነው።

በተለይም ወደ ምሁራኑ አምባ ጎራ ስንል የምናገኛቸው አፍቃሬ ኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያም አብዝተው ያሰቡ፣ አስበውም የተመራመሩ፣ ተመራምረውም በሰሯቸው በርካታ ስራዎች እውነቱን ቁጭ ያደረጉ አያሌ ሲሆኑ፣ አንዱም ዛሬ የምናስታውሳቸው ባለውለታችን ጁላይ 10 1919 ወደ'ዚህ ዓለም የመጡትና ጁን 24 2012 ከዚህ አለም የተለዩት አለም አቀፍ ምሁሩ ፕሮፌሰር ሰምነር (Claude Sumner, SJ) ናቸው።

በዜግነት ካናዳዊ፣ በምርጫቸው ኢትዮጵያዊ የሆኑት ፕሮፌሰር ሰምነር ከኢትዮጵያ ጋር የነበራቸው የማይበጠስ ቁርኝት የሚጀምረው ለ50 ጥቂት ፈሪ አመታት ወዳ ስተማሩበት፣ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከመጡበት 1953 ጀምሮ ሲሆን፤ ይህም በዘመን አይሽሬ ስራዎቻቸው ከመገለፁ ባሻገር እስከ'ለተ ሕይወታቸው ፍፃሜ ድረስ የአንገት ማተባቸው ሆኖ ዘልቋል። (ይህንን ሰፋ ባለ መልኩ ለመረዳት በቴዎድሮስ ኪሮስ የተጠቀሰውንና ከ"Ethiopian Review" (July 1994) ጋር ያደረጉትን ቃለ-መጠይቅ፤ እንዲሁም በዚሁ ሰው "Doing African Philosophy: Claude Sumner's Work on Ethiopian Philosophy" በሚል የተዘጋጀውን ጥናት ይመለከቷል።)

በተለይ የ'ኛኑ ፈላስፋ ወርቅዬ (ዘርዓ ያዕቆብ (1599–1692))ን እና ደቀ መዝሙሩ ወልደሕይወት (ምትኩ)ን፤ እንዲሁም ፍልስፍናቸውን (ሀተታዎች - ዝቅ ብለን የምንጠቅሳቸው ሥሜነህ "ሐተታ" የተባለው የፍልስፍና መንገድ አንድን ጉዳይ ደረጃ በደረጃ እየጠየቁ ጥልቅ ወደ ሆነ ምርምር የመግባትና በዚህም አንድ እውነተኛ እውቀት ላይ የመድረስ ሂደትን ያመለክታል።ያሉትን መያዙ ጠቃሚ ነው።) ለድፍን አለም ከማስተዋወቅ እና የፍልስፍናቸውን መሰረት (በተለይ "በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን የሕይወት ታሪኩንና የፍልስፍና ስራውን ብራና ዳምጦ፣ ቀለም በጥብጦ፣ በመጻፍ ያቆየልን ኢትዮጵያዊ አመክኗዊ (rational) ፈላስፋ" ስለመሆኑ እውቅናን ያገኘው ዘርአያዕቆብ ታላቅ ስራ መሆኑ የተመሰከረለትንና ተለይቶ የሚታወቅበትን "ሀተታ" ፈልፍሎ ከማውጣት አኳያ ያለምንም ተወዳዳሪም ሆነ ተፎካካሪ ተጠቃሽ የሆኑት ሰምነር በዚሁ ስራቸው አለም አቀፍ እውቅናን ማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሳይቀር የክብር ዶክተሬት ዲግሪን አግኝቷል። (በአለማችን የዘመናዊ ፍልስፍና ፈር ቀዳጅ የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ በተለይም የዘርዓያዕቆብ ፍልስፍና ነው የሚል ማጠቃለያ ላይ የደረሱት ሰምነር ኢትዮጵያን በተመለከተ በርካታ ስራዎችን ያከናወኑ ሲሆን፤ በተለይ Ethiopian Philosophy, vol. I: The Book of the Wise Philosophers, Ethiopian Philosophy, vol. II: The Treatise of Zara Yaecob and Walda Hewat: Text and Authorship፥ Ethiopian Philosophy, vol. III: The Treatise of Zara Yaecob and Walda Hewat: An Analysis, Ethiopian Philosophy, vol. IV: The Life and Maxims of Skandes, Ethiopian Philosophy, vol. V: The Fisalgwos, Classical Ethiopian Philosophy ስራዎቻቸው በቀዳሚነት ይጠቀሱላቸዋል።)

ሰምነር ልክ በዚሁ ዘመን በፈረንሳይ በዴካርቴስ እንደተጀመረው ሁሉ፤ ዘመናዊው የምክንያታዊነት (አመክኗዊነት?) ፍልስፍና በዘርአያዕቆብ አማካኝነት በአፍሪካ ተጀመረ (He argued that modern rationalist philosophy began in Africa with Zera Yacob at the same time that it began in France with Descartes.) የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስም በአፍሪካ፤ በተለይም በኢትጵያ ፍልስፍና ላይ የነበረውን የተዛባ የነጮቹን አለም አተያይ ፋርሽ አድርገዋል።

**ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተሳሰፉ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍናዎች በስነቃል (ተረትና ምሳሌ፣ በምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ በቃል ግጥም፣ በዘይቤዎች፣ በቅኔዎችና በወጎች ወዘተ)፤ መዝሙሮች፣ ኃይማኖታዊ ስነስርአቶች፣ ግለታሪኮች፣ የፀሎት መፃህፍት ... አማካኝነት እንደሚገለጡ አሳምረው የሚያውቁት ሰውየው የኢትዮጵያን ፍልስፍናና ተያያዥ ጉዳዮችን አይን ከሰበከት አገላብጠው የፈተሹ በመሆናቸው ፍሬያማነታቸው የተመሰከረላቸው ናቸው**

በካንሰር ህመም ምክንያት በ92 አመታቸው ከዚህ አለም በሞት የተለዩት ካናዳዊው የፍልስፍና ፕሮፌሰር ክላውድ ሰምነር ባደረጓቸው ዘርፈ ብዙና ሁሉን አቀፍ ጥናታቸው"Philosophical tradition, the main source of African philosophy." (የአፍሪካ ፍልስፍና ምንጭ የመፈላሰፍ ልማድ ነው) የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱ ሲሆን፤ በተለይም ኢትዮጵያን በተመለከተ፤

(ኢትዮጵያ የሁለቱም፤ ማለትም የተፃፈም ያልተፃፈም፣ ጥንታዊ እና ስር ነቀላዊ፣ መንፈሳዊና ገሳጭ፣ ህዝባዊና ግላዊ ፍልስፍናዎች መገኛ ነች። የተለያዩ የፍልስፍና አገላለፆች [ቋንቋዎች]፤ እንዲሁም፣ ዘመናዊ አስተሳሰብ የሚገኝባት ምድር ነች።) "Ethiopia therefore harbours both types of philosophy: oral and written, traditional and radical, sapiential and critical, popular and personal. It is the land of diverse expressions of philosophy and the birthplace of modern thought" (Sumner, 1998, African Philosophy, p. 333) በማለት ያሰፈሩት ኢትዮጵያና ፍልስፍናዋን በተመለከተ ሀሳብ በተነሳ ቁጥር ሁሌም ሳይጠቀስላቸው የማይታለፍ ድምዳሜያቸው ነው።

ከጥናቶቻቸውም ባለፈ በ1961 በአፍሪካ ሕብረት አዳራሽ በመገኘት ለመሪዎችና አጠቃላይ ታዳሚው "The Existence and Nature of African Philosophy—Problématique d'une philosophie africaine," በሚል ርእስ በወቅቱ ታዳሚውን እጅግ ያስደመመና እጅን ከንፈር ላይ ያስጫነ ጥናት ያቀረቡ ሲሆን፤ በዚሁ ጥናታቸውም የኢትዮጵያን ፍልስፍና (እሳቸው written philosophical literature of Ethiopia ያሉት) እና መሰረቱን ከፍ አድርገው ማሳየታቸውን በThe Proverb and Oral Society (1999) ስራቸው ላይ ለንባብ አብቅተውት እናገኛለን።

ሰምነር በእነዚህ ጥልቅ የምርምር ስራዎቻቸው አማካኝነት ሶስት አበይት ተግባራትን ማከናወናቸው የሚነገርላቸው ሲሆን፤ አንዱም ግዕዝን በተዋጣለት የእንግሊዝኛ ትርጉም አማካኝነት ለአንባቢያን፤ በተለይም በዘርፉ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ ሰዎች፤ እንዲሁም ለአካዳሚው ማህበረሰብ ማቀብላቸውና የኢትዮጵያን ፍልስፍና ለአለም አደባባይ ማብቃታቸው (በClassical Ethiopian Philosophy መጽሐፉ መጽሐፈ ፊሳልግዎስ፣ አንጋረ ፈላስፋ፣ የስክንድስ ህይወትና አባባሎቹ፣ ሀተታ ዘርዓያዕቆብ እና ሀተታ ወልደ ሕይወት የፍልስፍና ስራዎችን ከግዕዝ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተርጉመው


ፕሮፌሰር ክላውድ ሰምነር

አሳትመዋል፡፡) መሆኑ ስለ እሳቸው በተሰሩ ጥናትና ምርምር ስራዎች ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል። ("Cultural Heritage and Contemporary Change Series II. Africa, Volume 15"ን ተመልከት። እድሉ የሚገኝ ከሆነም የሰምነር ስራዎች ብርቅና ድንቅ የሆኑበትን፣ በአለማችን ድንቅ የተሰኘውንና አሜሪካዊውን Library of Congressን መጎብኘት፤ እንዲሁም The Source of African Philosophy: The Ethiopian Philosophy of Man, እና Oromo Wisdom Literature (ቅፆች ያሉት) መመልከት ይቻላል።)

ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፉ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍናዎች በስነቃል (ተረትና ምሳሌ፣ በምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ በቃል ግጥም፣ በዘይቤዎች፣ በቅኔዎችና በወጎች ወዘተ)፤ መዝሙሮች፣ ኃይማኖታዊ ስነስርአቶች፣ ግለታሪኮች፣ የፀሎት መፃህፍት ... አማካኝነት እንደሚገለጡ አሳምረው የሚያውቁት ሰውየው የኢትዮጵያን ፍልስፍናና ተያያዥ ጉዳዮችን አይን ከሰበከት አገላብጠው የፈተሹ በመሆናቸው ፍሬያማነታቸው የተመሰከረላቸው ናቸው።የመቀሌ ዩኒቨርሲቲው የፍልስፍና መምህሩር ብሩህ አለምነህ ስራዎችንም መመልከት ስለ ሰምነር ሌላው የመረጃ ምንጭ ነው።

ሰምነር ብዙ የሰሩ ብቻ ሳይሆን ብዙ የተባለላቸውም ምሁር ናቸው። በአበረከቱት የማይተካ አስተዋፅኦ ምክንያት ኢትዮጵያዊ ዜግነት ለማግኘት የቻሉት ፕሮፌሰር ሰምነር በጥንታዊ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ዙሪያ የሚያጠነጥኑ በርካታ መጻሕፍትን (በቅፆች)፣ ጥናታዊ ጽሑፎችንና መጣጥፎች አሳትመዋል። በተጨማሪም የኦሮምኛ የሥነ-ቃልና የሥነ-ተረት ፍልስፍናዊ አንደምታን የሚያትቱ ሁለት ድርሳናትን ጽፈዋል። "ዕድሜ ለፕሮፌሰር ሰምነር፣ ዛሬ በአፍሪካ ፍልስፍና (African philosophy) ዙሪያ የሚጻፉ መጻሕፍት የዘርዐ ያዕቆብን እና የወልደሕይወትን ሥም ሳይጠቅሱ አያልፉም።

ኢትዮጵያ ገና ያልተጠኑ የበርካታ ጥንታዊ ሥነጽሁፎች ባለቤት፤ ዘመናትን ያስቆጠሩ ቃላዊና የጽሁፍ ፍልስፍናዎች ምድር ወዘተ መሆኗን አጥብቀውና ደጋግመው የሚናገሩት ሰምነር የመጪው ዘመን ተመራማሪዎች ትኩረታቸውን በዚሁ ላይ እንዲያደርጉና እውነቱ ላይ እንዲደርሱም ሳይሳሱ ይመክራሉ።

ከአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች በተለየ መልኩ በርከት ያሉ የፍልስፍና ስራዎችን በመስራት በቀዳሚነት የምትጠቀሰው ኢትዮጵያ፤ በጥንታዊው የግእዝ ቋንቋ ከተጻፉት የፍልስፍና ስራዎቿ መካከል አብዛኞቹ እንኳን ሊጠኑ ገና ምናቸውም አልተነካም የሚሉት የፍልስፍና ምሁሩ እነዚህ ሁሉ በአግባቡ ከተጠኑ ኢትዮጵያ፤ እንደ አጠቃላይም የአፍሪካ ማንነትና ፍልስፍና አደባባይ ይወጣል የሚል ፅኑ እምነት አላቸው።

በዚሁ ጉዳይና የሰምነር ባለውለታነት ላይ ሀሳባቸውን ለንባብ ያበቁ ብሎገር ("ስሜነህ ጌታነህ@ DireTube" በሚል መለያ የሚጽፉ)፤

በኢትዮጵያ የሥነጽሁፍና ታሪክ ውስጥ በመጀመሪያው ክፍል እንደተጻፈ የሚነገርለት የመጀመሪያው የፍልስፍና የጽሁፍ ስራ መጽሐፈ ፊሳልግዎስ (physiologus) ይባላል።ይህ የፍልስፍና ስራ በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተጻፈ የሚነገርለትን የጥበብ ስራ ከግሪክ ወደ ግእዝ ቋንቋ በመተርጎም የተሰራ ሲሆን ትርጓሜውም ተራ ሳይሆን ከኢትዮጵያ የባህልና የቋንቋ አውድ ጋር በማዛመድ የተሰራ ነው።ፊሳልግዎስ በአምስተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ወይም አጋማሽ አካባቢ ከፍተኛ የመጽሐፍ ክምችት በሚገኝበት ምናልባትም በግብጽ ሀገር በሚገኝ ገዳም ውስጥ በሚኖር ኢትዮጵያዊ ጸሐፊ እንደተጻፈ ይገመታል።ፈላስፋው ሰምነር የጥንታዊ ድርሳናት ተመራማሪው (philologist) ፍሪትዝ ሆሜል (Hommel) በ1877 ዓ.ም በለንደን፣ ፓሪስና ቬና ቤተመዛግብት ውስጥ የሚገኙ የግእዝ ብራና ፊሳልግዎስ መጻህፍትን ከጀርመንኛ ትርጓሜው ጋር በማገናዘብ ካዘጋጀው የተስተካከለ ቅጽ (critical edition) ላይ የተረጎመው ሲሆን ከካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ የ1951 ጣልያንኛ ትርጉም ጋርም አመሳክሮታል።ፊሳልግዎስ ለመጽሐፉ ደራሲ የተሰጠ ስያሜ ሲሆን ይህም እንስሳትን፣ ዕጽዋትናና የማዕድናትን ምንነት የሚገልጽና በተምሳሌት (symbolism) የሚያስቀምጥ ነው፡፡

በማለት ያሰፈሩትን፤ እንዲሁም:-

በኢትዮጵያ የስነጽሁፍ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ግምት በሚሰጠውና ሁለተኛው ክፍለ ዘመን በመባል በሚታወቀው የአጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግስት (1434-68)፤ "መጽሐፈ ፈላስፋና የስክንድስ ሕይወትና አባባሎቹ" የተባሉ ሁለት የፍልስፍና መጻህፍት ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉመዋል።ምናልባት "እነዚህ ትርጉም ስራዎች እንዴት የኢትዮጵያ ፍልስፍና የሚል ስያሜ ሊሰጣቸው ቻለ?" የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል።ሰምነር እንደሚለው፤ ምንም እንኳ ስራዎቹ ትርጉም ቢሆኑም ኢትዮጵያውያን ዝም ብለው እንደ ወረደ አይተረጉሙም፤ የራሳቸው የሆነ የአተረጓጎም ስልት ስላላቸው ትርጉሞቻቸው ኢትዮጵያዊ አሻራን ይይዛሉ። "Ethiopians never translate literally: they adapt, modify, add, subtract. A translation therefore bears a typically Ethiopian stamp" (ኢትዮጵያውያን በትርጉም ሂደት ላይ ከራሳቸው ባህልና አውድ ጋር ለማዋሃድ ሆን ብለው የማወራረስ፣ የመቀነስና የማሻሻል ባህል ስላላቸውና ፍጹም ኢትዮጵያዊ አሻራ እንዲኖረው በማድረግ ስለሚተረጉሙ ነው፡፡)

በማለት ስለ ሰምነር የሰጡትን ውለታ ከፋይ ማብራሪያ እዚህ መጥቀሱ የባለውለታውን የእውነትን ፍለጋ ሩጫ ያሳያልና አንባቢያን ሙሉውን ጽሑፍ ፈልገው ቢመለከቱት ያተርፋሉ ባይ ነን።

በአጠቃላይ በጥንታዊት ኢትዮጵያ (በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን (1599-1692)) የትምህርት ሥርዓት፤ በንባብ ቤት፣ በዜማ ቤትና በቅኔ/ሰዋስው ቤት ያለፈ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ሲሆን እርሱ በነበረበት ዘመን የነበሩ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነምግባራዊ አስተሳሰቦችን በአመክኗዊ ሐተታ (rational inquiry) በመታገዝ ይመረምርና ይተች የነበረው ፈላስፋ ዘርዓያዕቆብ ("ዘርዓ ያዕቆብ የፍልስፍና ትምህርት ቤት" የሚል ተቋም ከፍተው ፍላጎት ያላቸውን እያስተማሩ ያሉትን በዚህ አጋጣሚ ማመስገን ያስፈልጋል)፤ እንዲሁም ደቀመዝሙሩ ወልደሕይወትና ስራዎቻቸው (ሀተታዎቻቸው) በፕሮፌሰር ክላውድ ሰምነር አማካኝነት ተፈትሸውና ያሉበት የፍልስፍና ደረጃ ተመርምሮ ይዘታቸው ብቻ ሳይሆን ፋይዳና ቀዳሚነታቸው ሁሉ ተረጋግጧል። ጥናቶች በተደጋጋሚ እንደሚሉት ሁሉ "ዛሬ የዘርዓያዕቆብ ፍልስፍና በዓለም ሊታወቅ የቻለው ካናዳዊ ዜግነት ባለው ፕሮፌሰር ክላውድ ሰምነር አማካኝነት ነው፡፡" ይህም ሰምነርን በዘርፉ የምሁራን ሁሉ ቁንጮ (በተለይ ያልተነካውን በመንካት) ከማድረጉም በላይ፤ መታወቂያቸውም ሊሆን በቅቷል (ስለሳቸው ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ሁሉ Best known by Ethiopian philosophy እንደሚሉት)።እኛም ለሰሩት ስራ ላበረከቱት አስተዋፅኦና ላፈሯቸው ፍሬዎች ማስታወሻ ይሆን ዘንድ ይህንን መዘክር ስናበረክት ደስታ እየተሰማን ሲሆን፤ ወደ ፊትም ሆነ አሁን ከስራዎቻቸው ጋር ትውውቅ ለሚፈጥሩ ሁሉ መልካሙን እንመኛለን።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

ረቡዕ
አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ኢትዮጵያውያን ወጣት አትሌቶች በካሊ እያንጸባረቁ ነው

**ቦጋለ አበበ**

አስደናቂ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናን አሰናድታ ከሳምንት በፊት ድግሷን ያጠናቀቀችው ኦሪገን ከ179 አገራት 1700 አትሌቶችን በእንግድነት ተቀብላ ሸኝታለች። በታላቁና ደማቁ ዝግጅቷም 29 አገራት የወርቅ ሜዳሊያ ይዘው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል። 40 አገራት ባዶ እጃቸውን አልተመለሱም። አንድና ከዚያም በላይ ሜዳሊያዎች ወስደዋል፡፡ 3 የዓለም ክብረወሰኖች እንዲሁም 13 የዓለም ቻምፒዮና ክብረወሰኖችም ተሰብረዋል። 150ሺ የስታድዬም ተመልካቾች፣ ከ400ሺ በላይ የማህበራዊ ሚዲያ ተከታዮች፣ ከ41 ሚሊዮን በላይ የቪዲዮ ተመልካቾች የኦሪገንን ድግስ አድምቀው ከትናንት በስቲያ ሌሊት ጀምሮ ፊታቸውን ከሰሜን አሜሪካ ወደ ደቡብ አሜሪካዊቷ አገር ኮሎምቢያ አዙረዋል። ካሊ ከሰኞ ሌሊት ጀምሮ ለቀጣይ ጥቂት ቀናት የአትሌቲክስ ቤተሰቡ አይን የሚያርፍባት ከተማ ነች።

የዓለም ከ20 አመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና በካሊ መካሄድ ሲጀምር ኢትዮጵያውያን ወጣት አትሌቶች የበላዮቻቸው ባለፉት ሳምንታት በኦሪገን እንደደመቁት ሁሉ ከውድድሩ የመጀመሪያ ቀን አንስቶ በካሊ ማንጸባረቅ ጀምረዋል።

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በኦሪገኑ የዓለም ቻምፒዮና በወንዶች 5ሺ ሜትር የገጠማቸው አስደንጋጭ ውጤት ካሊ ላይ አልተደገመም። የነገ የርቀቱ ተተኪ የሆኑ ወጣቶቹ ኮከቦች በርቀቱ በአዋቂዎች ኢትዮጵያ ያጣችውን የወርቅ ሜዳሊያ በማጥለቅ የቻምፒዮናውን





አትሌት አዲሱ ይሁኔ በ5ሺ ሜትር ወርቅ ሲያጠልቅ ጺዮን አበበ በ3ሺ ሜትር የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ሆናለች፣

ጉዞ በድል ጀምረዋል። እጅግ አስደናቂ ፉክክር በታየበት በዚህ ውድድር ኢትዮጵያውያን ወጣት አትሌቶች ከዓለም የርቀቱ ከዋክብት ወጣቶች ጋር እልህ አስጨራሽ ፍልሚያ አድርገው ለድል በቅተዋል። በርካታ አገራት በርቀቱ ጠንካራ ተፎካካሪ ሆነው ብቅ ባሉበት ውድድር ኢትዮጵያውያኑ ወጣት አትሌቶች አዲሱ ይሁኔና ገበየሁ በላይ በድንቅ የቡድን ሥራ እንዲሁም በራስ መተማመን ያሳዩት ጀግንነት አስደናቂ ነበር። ሁለቱም አትሌቶች ከኬንያ፣ ዩጋንዳና ኤርትራ አትሌቶች ብርቱ ፉክክር የገጠማቸው ቢሆንም ውድድሩን በራሳቸው መንገድ ተቆጣጥረው አገራቸውን ለድል አብቅተዋል። ሁለቱም ወጣት አትሌቶች ተከታትለው ለመግባት ያደረጉት ጥረት ባይሰምርም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ፍጹም በራስ መተማመን ይነበብበት የነበረው አትሌት አዲሱ ይሁኔ በ14:03.05 ወርቁን ማጥለቅ ችሏል። ወርቅ ለማጥለቅ ድንቅ ፉክክር ያደረጉት ኤርትራውያኑ አትሌቶች የኢትዮጵያውያን ድንቅ አትሌት የአጨራረስ ብቃት መመከት ባይችሉም የብርና የነሐስ ሜዳሊያውን ከኬንያና ዩጋንዳ አትሌቶች መንጠቅ ችለዋል። በዚህም መርሃዊ መብርሃቱ በ14:03.33 ሁለተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ ሃብቶም ሳሙኤል በ14:03.67 ሰዓት ሦስተኛ ሆኖ ውድድሩን ፈጽሟል። ሜዳሊያ ውስጥ ለመግባት ትልቅ ጥረት ያደረገው ኢትዮጵያዊው አትሌት ገበየሁ በላይ በ14:04.55 ሰዓት አራተኛ በመሆን የዲፕሎማ ደረጃ ይዞ አጠናቋል። ባለፈው አመት በናይሮቢ በተካሄደው ተመሳሳይ የዓለም ከ20 አመት በታች ቻምፒዮና አዲሱ ይሁኔ አራተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ ኤርትራውያኑ አትሌቶች አምስተኛና ስድስተኛ ደረጃን ይዘው ማጠናቀቃቸው ይታወቃል።

በተመሳሳይ ዕለት በሴቶች መካከል በተካሄደው የ3ሺ ሜትር የፍጻሜ ውድድርም ኢትዮጵያ የብር ሜዳሊያ ያገኘችበትን ውጤት አስመዝግባለች። ከውድድሩ አጋማሽ ጀምሮ ኬንያውያን አትሌቶች ሌሎቹን ተፎካካሪዎች ከውድድር ውጪ ለማድረግ ያሳዩትን ጥረትና እቅድ ለማክሸፍ የታገለችው ጺዮን አበበ ያደረገችው ትልቅ ትንቅንቅ በመጨረሻም የብር ሜዳሊያ ለማጥለቅ አብቅቷታል። ኬንያዊቷ ቤቲ ቼላንጋት አስደናቂ የአጨራረስ ብቃቷን ባሳየችበት ፉክክር 9:01.03 በሆነ ሰዓት ወርቅ ከማጥለቅ ያገዳት አልነበረም። ይህች ጠንካራ ኬንያዊት የአገሯን ልጅ ናንሲ ቼሮፕን አስከትላ ለመግባት ያደረገችውን ጥረት ፉርሽ ያደረገችው ጺዮን አበበ የብር ሜዳሊያውን በ9:03.85 ሰዓት ወስዳለች። በ9:05.98 የነሐስ ሜዳሊያውን ናንሲ ቼሮፕ ስታጠልቅ እሷን ተከትላ ኢትዮጵያዊቷ ብርቱካን ወልዴ በ9:18.20 ሰዓት አራተኛ ደረጃን ይዛ አጠናቃለች።

በወጣት አትሌቶች መካከል በካሊ የሚደረገው ፉክክር ዛሬ ሌሊት ሲቀጥልም ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በ1500 ሜትር ወንዶች እንዲሁም በስምንት መቶ ሜትር ሴቶች በሚያደርጉት የፍጻሜ ፍልሚያ ተጨማሪ ሜዳሊያዎችን ያስመዘግባሉ ተብሎ ይጠበቃል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የሽልማት መርሐግብር ሜዳሊያ ላመጡ አትሌቶች

በአሜሪካ ኦሪገን በተካሄደው 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና የተመዘገበውን አኩሪ ድል በማስመልከት የአትሌቶች የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል መርሐ-ግብር በብሔራዊ ቤተ-መንግሥት በተካሄደበት ወቅት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴን ጨምሮ የተለያዩ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ታዋቂ ግለሰቦች እና የልዩ ልዩ ማህበረሰብ አካላት ተገኝተዋል።

በሻምፒዮና አኩሪ ድል ላስመዘገቡ አትሌቶች እና ሌሎች የልዑካን ቡድን አባላት ከ50 ሺህ ብር እስከ 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር የሚደርስ ሽልማት ተበርክቷል። ለተሰንበት ግደይ በ10 ሺህ ሜትር የመጀመሪያውን ወርቅ በማስገኘቷ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር እና በአምስት ሺህ ሜርት ላሳየችው ውጤታማ የቡድን ሥራ 500 ሺ ብር በድምሩ የሁለት ሚሊዮን ብር ተሸላሚ ሆናለች።

በሴቶች ማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ ያስገኘችው አትሌት ጎይተቶም ገብረሥላሴ እና በወንዶች ማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ ያስገኘው ታምራት ቶላ እያንዳንዳቸው የአንድ ሚሊዮን 750 ሺህ ብር ተሸላሚ ሆነዋል። በ1 ሺህ 500 ሜትር የብር ሜዳሊያ እና በ5 ሺህ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ያስገኘችው ጉዳፍ ጸጋይ በልዩ ሁኔታ የሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ተሸላሚ ሆናለች።

በወንዶች ማራቶን ሁለተኛ ደረጃን ይዞ በማጠናቀቅ የብር ሜዳሊያ ያስገኘው ሞስነት ገረመው አንድ ሚሊዮን ብር፣ በ3 ሺህ መሰናክል የብር ሜዳሊያ ያስገኘችው ወርቅውሃ ጌታቸው አንድ ሚሊዮን ብር እንዲሁም በ3 ሺህ መሰናክል የብር ሜዳሊያ ላስገኘው ለሜቻ ግርማ የአንድ ሚሊዮን ብር ተሸላሚ ሆነዋል። በሻምፒዮናው የነሐስ ሜዳሊያ ላመጡ አትሌቶችም የ700 ሺህ ብር ሽልማት ተደርጎላቸዋል።




በሌላ በኩል 10 ሜዳሊያዎችን በማምጣት ከዓለም 2ኛ ከአፍሪካ 1ኛ በመሆን በድል ለተመለሰው ጀግናው የአትሌቲክስ ቡድናችን «አንድ ሆነን እንስራ፤ ኢትዮጵያ ታሸንፍ» በሚል መሪ ቃል የምስጋና እና የክብር መስጠት መርሐ-ግብር በማዘጋጀ ቤት የተለያዩ የፌዴራልና የከተማ አስተዳደሩ የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ካቢኔ ሐምሌ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው አስቸኳይ ሰብሰባው በ18ኛው ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድር እንደየደረጃው ሜዳሊያ ላመጡ አትሌቶች በሽልማትነት እንዲሰጥ በወሰነው መሠረት በውድድሩ ላይ የወርቅ ሜዳሊያ ላመጡ ለእያንዳንዳቸው ስፋቱ 500 ካሬ ሜትር፣ ለብር ሜዳሊያ 350 ካሬ ሜትር እንዲሁም የነሐስ ሜዳሊያ ላመጡ 250 ካሬ ሜትር የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በምስጋናነት ተበርክቶላቸዋል። ከተማ አስተዳደሩ ከዚህም በተጨማሪ በሻምፒዮናው ላይ ለተሳተፈው የልዑካን ቡድን በጥቅሉ የ10 ሚሊዮን ብር ሽልማት በጥሬ ገንዘብ አበርክቷል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በምስጋናና ክብር መስጠት መርሐ ግብር ባደረጉት ንግግር «ኢትዮጵያ የልጆቿ ገፅ ናት» ብለዋል። በድላችሁ ኢትዮጵያን ገፅታዋን ልታድሱ፣ ክብሯን በድል ልትገልጡ፣ ሰንደቃችሁን አትማችሁ ኢትዮጵያን አስቀድማችሁ በ18 ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ከፊት ስላቆማችሁን ደስ ብሎናል እንኳን ደስ አለን ብለዋል። እኛ ኢትዮጵያውያን ፈተና የማይረታን፣ ይልቁንም የሚያፀናን፣ መሰናከል የማያቆመን ይልቁንም አንድነታችንን የሚያጠናክሩን ሕዝቦች መሆናችን ነጋሪ እንደማያስፈልግ ይጠቅሳሉ።

የሥነ ልቦና ስሪታችን ማሸነፍ፣ በማሸነፍ ውስጥ አገርን ከፍ ማድረግ አንገታችንን ቀና አድርገን በክብር አደባባይ መጓዝ ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በ18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በድል የተመለሳችሁ እናንተ የሁላችንም የክብር ጌጥ ናችሁ ብለዋቸዋል።

የኢትዮጵያ በቀጣይ በምታደርገው ውድድሮች አትሌቶችን የሜዳሊያ ብዛት ከፍ ለማደረግ እንደሚሠራ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ በቤተመንግሥት በተካሄደው የምስጋና መርሃ ግብር ላይ ተናግራለች።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ፣ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተለያዩ ጫናዎች ውስጥ ሆነው ከፍተኛ ድል ማስመዝገባቸውን ገልፃለች። ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ስሟ ከፍ እንዲል ያደረጉ አሁን ላይ የተገኙ ጀግና አትሌቶች የቀድሞ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የትውልድ ቅብብሎሽ ውጤት ናቸው ብላለች።

የአትሌቲክስ ልዑካን ቡድን በኦሪገን ቆይታው የተሳካ ጊዜን እንዲያሳልፍ አስተዋፅዖ ላደረጉ ተቋማትና ግለሰቦች ፕሬዚዳንቷ ምስጋናዋን አቅርባለች። በኦሪገን ኢትዮጵያ አሸንፋለች ያለችው ደራርቱ በቀጣይ በሚደረጉ ዓለምአቀፋዊ ውድድሮችም የኢትዮጵያውያን አትሌቶችን የሜዳሊያ ብዛት ከፍ ለማድረግ ይሠራል ብላለች።

በአሜሪካ ኦሪገን የተካሄደው 18 ኛውን የአትሌቲክስ ሻምፒዮና ውድድር በ 4 የወርቅ፣ 4 የብር፣ 2 የነሐስ፣ በድምሩ 10 ሜዳሊያዎችን በመውሰድ ከዓለም አዘጋጇን አገር አሜሪካንን በመከተል የ2ኛ ደረጃን በመያዝ ማጠናቀቁ ይታወቃል።

Telegram https://t.me/ministry ofcultureandtourism

Facebook https://www.facebook.com/cultureandsportethiopia